# መናፍቅነት በዓለም

# ከትናንት እስከዛሬ

(ታሪካዊ ዳሰሳ)

ክፍል አንድ

ከመምህር ሳሙኤል እሸቴ
ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል የሰ/በ/ት/ቤት ወንጌል ጉባኤ

1995 ዓ.ም

12 95 80
31227
Addis Ababa
Ethiopia

www.ethiopianorthodox.org

የአዘጋጁ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።
All rights reserved

## ምስጋና

መጽሐፉን በማንበብ አስተያየት ለሰጡኝ ለዲ. ያሬድ አደመ፣ ለዲ. ዘሪሁን ሙላቱ፣ ለመምህር ሰሎሞን በቀለ እና ሰሎሞን ቶልቻ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

## አበርክቶት

ለምወዳት እናቴ ለተዋበች አባቡ በዛብህ እና የመጀመሪያ መጽሐፌን ሙሉ ወጪውን በመሸፈን ላሳተመችልኝ አሜሪካን አገር ለምትኖረው ለእህቴ ትርንጉ መኮንን በቀለ።

## መታሰቢያነቱ

በወንጌል ኮትኩተው ላሳደጉኝ ለመልአከ ገነት አባ ተስፋ ማርያም፣ አሁን ላለሁበት ማንነቴ መሠረት ለሆኑት ለሲዳሞ ሀ/ስብከት ሥራ አስኪያጅ መ/ር ኃ/ሥላሴ ይግዛው፣ ለመልአከ ምህረት ጳውሎስ ቀጸላ እና ለቦሬ ደ/ገነት ቅድስት ማርያም ቤተ/ክርስቲያን ትሁንልኝ።

የአዘጋጁ አድራሻ፡-
ፖ.ሣ.ቁ.፡- 14412
Email - Samuel_Eshetu@Yaho.com.
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

## ማውጫ

መግቢያ.........................................................................................
ምዕራፍ አንድ.........................................................................................
1.1 መንደርደሪያ..... ......................................................................
1.2 ቤተክርስቲያን ማን ናት? .................................................
1.3 ቤተክርስቲያን ምን ታምናለች? ...........................................
ምዕራፍ ሁለት.........................................................................................
የመናፍቃን ማንነት በዘመናት እይታ.................................................
2.1 ከጌታ ዘመን እስከ 570 ዓ.ም. ..............................................
2.1.1 ሀራጥቃዎች (Judoxin)..................................................
2.1.2 ናዝራውያን (Nazarenes)...............................................
2.1.3 ኢቦዮናውያን(Ebonites).................................................
2.1.4 ኤልሳቃውያን (Elkesaites)............................................
2.1.5 ግኖስቲክስ (Gnostics)....................................................
2.1.6 መቅያኒዝም (Mareianism)..............................................
2.1.7 ሞንታኒዝም (Montainism)..............................................
2.2 አዕራረ ስላሴ (Anti-Trinity)..................................................
ምዕራፍ ሶስት.........................................................................................
መናፍቅነት ከ570 እስከ 1517....................................................
3.1 የሮም ካቶሊክ የስህተት ትምህርቶች.................................
3.2.1 ፊሊክዌ (Filioque) ሁለትዮሽ ሥርፀት.......................
3.2.2 አስቀድሞ መወሰን (Pre destination).........................
3.2.3 መካነ ንስሐ (Pergatory)..............................................

www.ethiopianorthodox.org

3.2.4 ስለ ጋጋው ፍፁምነትና ስግደት እንደሚገባው.......

3.2.5 የቁርባን ሥርዓት.......

3.2.6 የኢኮኖላትሪያ (Iconoclastic) (ቅርፅ አክብሮት) .......

ምዕራፍ አራት.......

መናፍቅነት ከ1517 - 1750.......

4.1 ማርቲን ሉተርና ትምህርተ ክህደቱ.......

4.2 ጆን ካልቪንና ትምህርተ ክህደቱ.......

ምዕራፍ አምስት.......

መናፍቅነት ከ1750 እስከ 19... .......

5.1 ሁለቱ መነሻዎች.......

5.2 ፕሮቴስታንቲዝምና ክፍልፋዩ.......

5.2.1 ወንጌላውያን (Evangeust) .......

5.2.2 መጥምቃውያን (Ana baptist) .......

5.2.3 ካሪዝማቲክ (ጴንጤቆስጤዊነት)

5.3 የሐዋርያት እምነት ድርጅት (Only Jesus) .......

5.4 ሞርሞኒዝም (The later days of Saints of Church of Jesus Christ) .......

5.5 ዓለም አቀፍ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን (World Wide Church of God) .......

5.6 ዩኒፊኬሽን ቸርች (Unification Church) .......

5.7 ዩኒቲ እስኩል ኦፍ ክርስቲያን.......

5.8 ስፕሪቲዝም (Spritizim) .......

5.9 የይሖዋ ምስክር (Johova Wittness).......

ማጠቃለያ .......


# መግቢያ

የዚህ መጽሐፍ መሰረታዊ መልዕክት በተለያዩ ጊዜ ተነስተው ቤተክርስቲያንን የተዋጉትንና እየተዋጉት ያሉትን የስህተት ትምህርት አስተማሪዎችንና የትምህርትታቸውን ምንነት ለዚህ ትውልድ ሊረዳው በሚችለው መንገድ ማቅረብ ነው።

የስህተት ትምህርቱን እንቅስቃሴ በአራት ዘመን ተከፍሏል። እርሱም፡-

1. ከጌታ - 570
2. ከ570 - 1570
3. ከ1570 - 1750
4. ከ1750 - 19... ያለ ሲሆን፣

በእነዚህ ዘመናት በዓበይት መናፍቅነት የተነሱትን ከ35 በላይ ሰዎችና የመናፍቃን ድርጅቶችን አስተምሮዎቻቸውን አሁን በምን ይዞታ እንዳሉ እንቃኝበታለን።

መጽሐፍ ቀጣይነት ያለው ነው። በመጀመሪያ የስህተት ትምህርቱ በዘመናችን እንደአሸን እየፈላ በመሆኑ የዚህን ስህተቶ ለመግለጥ መጽሐፉ ይቀጥላል። ሁለተኛው የህትመት ወጭ በመናሩና የተገልጋዩ አቅም በማነሱ ምክንያት ለሁለትና ለሶስት ክፍሉ በተከታታይነት ማቅረቡ እንደ ጥሩ መፍትሔ ተመልክቼዋለሁ።

በመሆኑም አንባቢ መጽሐፍን እንዲጠቀምበትና እምነቱን እንዲያፀና እየመከርኩ ስለመጽሐፉ የሚቀርበውን ገንቢ አስተያየት ለመቀበልም ዝግጁ ነኝ።


መ/ር ሳሙኤል እሸቱ
የመ/ጸ/ቅ/ሥላሴ ካቴድራል
የስብከተ ወንጌል ክፍል ኃላፊ


www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ አንድ

## 1.1 መንደርደሪያ

"አያውቁም፣ አያስቡም፣ እንዳያዩ አይኖቻቸውን፣ እንዳያስተውሉም ልቦቻቸውን ጨፍነዋል። በልቡም ማንም አያስብም ግማሽዋን በእሳት አቃጥያለሁ በፍምዋል ላይ እንጀራን ጋግሬአለሁ። ሥጋም ጠብሼ በልቻለሁ የቀረውንም አስፀያፊ ነገር አደርጋለሁን? ለዛፍስ ግንድ እሰግዳለሁን? እንዲልም እውቀትና ማስተዋል የለውም። አመድ ይበላል የተታለለ ልብ አስቶታል፣ ነፍሱን ለማዳን አይችልም ወይም በቀኝ እጄ ሐሰት አለ አይልም" (ኢሳ. 44፥18-20)።

ነቢዩ እንደተናገረው በዘመናችን ብዙዎች ሀሰትን በእጃቸው ይዘው እውነት እንዲሰሩና እንደያዙ የሚያውጁበት ግዜ ነው። ዓለማችን ከመክፋቷ የተነሳ በዘመናችን በክርስትናው ስም የተሻሩው ይፈፀም ዘንድ ብዙ አሳቾች ተነስተዋል። እነዚህም ጽድቅን የሚቃናቀኑ የክፋት ሥራዎች የበግ ለምድ ለብሰው በመንጋው መካከል የሚሄዱ ተኩላዎች ለጥፋት ልጅ (Anti-Christ) መንገድ ጠራጊ ሆነው ስህተቶቻቸውን የዓመፅ ምስጢራቸውን እየሰሩ ይታያል (2ተሰ. 2፥7)።

መናፍቅነት የሥጋ ሥራ ነው። ለዚህም ነው ዛሬ የመናፍቅነት እንቅስቃሴን ሁሉ ከኃጢያት ሥራ ጋር እንዲዛመዱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደሆኑ በማስመሰል የጥፋት ግብሬቸውን እሚፈፅሙት ለመጥቀስም፦



www.ethiopianorthodox.org

በአሜሪካን ሀገር በብዙ ቦታዎች ቅርንጫፍ እንዳለው የሚነገርለት ፔንቴኮስቲካል ቤተክርስቲያን የሚባለው ባለቤት እውቅ 36 ስባኪያኑ በየወሩ ለ30 ጥንድ ግብረ ሰዶማዊ ተጋቢዎች በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ብለው ጋብቻን ይፈጽማሉ። ይህን ድፍረትና ነውረት ሁሉ ሊገነዘብ ይገባል። ነገ ወደዚህች ሀገር መምጣቱ አይቀርምና።

ኤፒስኮፓል ቸርች የሚባለው ድርጅትም ሌዝቢያን (ሴት ለሴት ተጋቢዎች) ለሆኑ 4 ሴቶች የቅስና ሹመት መስጠቱንና የየጸሎት ቤት ኃላፊ እንዳደረጋቸው ጠቅሷል። Christian today ed. Aug. & Sep. 1998

በግንቦት ወር 1994 (May 6, 2002) የታተመው ኒዊስ ዊክ (Newsweek) ለሮም ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የተነሳውን ሀሜትን የመደፈርና የግብረ ሰዶማዊነት ችግር ባተተበት ጽሑፍ "The best guess is that between 35 and 50 percent of Roman Catholic Prists are homo sexual" በጥሩ ግምት ከ35-50 በመቶ የሚሆኑ የሮማ ካቶሊክ ቀሳውስት ግብረ ሰዶም ፈፃሚዎች ናቸው ይላል።

መጽሔቱ ከዚህ ጋር ብዙ በምዕራብ ዓለም ያሉ የእምነት ድርጅቶች ይህንን እንደሚደግፉና ኤፕስኮፓል ቀሳውስት የሆኑት ሬቨረንድ ሚካኤል ኦፕኪንስን እና ጆን ባርድ ሌይ ጋብቻቸውን (ግብረ ሰዶማዊ) በእምነት ድርጅታቸው ሲፈጽሙ ምስሉን አውጥቷል።

እንዲሁም የእምነት ቃል (Word of faith) የብልጽግና ወንጌል፣ የአዲስ ዘመን እንቅስቃሴ በሀገራችን ሳይቀር በአንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆኖዋል። በሌሎቹ ኑፋቄ እነርሱ መጨመራቸውን ማለት ነው።



እዚህ ሀገራችን የእምነት ቃል (Word of faith) እና የአሸናፊ መቅደስና መሰሎቻቸው የመገለጥ፣ በራእይ መታመን፣ ከአካል ውጭ ጉዞ (our of body experience) ከሌላው ዓለም በሌላ ጫፍ መገናኘት (dimension) የሚሉና በተለይም ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል ስለእምነት "እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጠን የማናየውንም ነገር የሚያስረዳን ነው። ለሽማግሌዎች የተመሰከረላቸው በዚህ ነውና" (ዕብ. 11፥1-2) በማለት ያስተምረናል። ነገር ግን እነዚህ የእምነት ድርጅቶች "እምነታችን በእምነት ላይ እንጂ በእግዚአብሔር መሆን የለበትም" ይላሉ። የሚያስፈጫቸው ጽሁፎች እንደሚጠቁሙት እምነት በእምነት ላይ የሚለውን እንዲህ ይገልጡታል።

- አንድ ነገር በል (Say it)
  ተናገረው አንጸ አፍህ ይሆንልሃል ከአንዴ በላይ መጸለይ አይገባህም ይላሉ። (ሳትታክቱ ጸልዩ ለእነርሱ ዋጋ የለውም")

- አድርገው (Do it) እርምጃ ውሰድ ተቀበል

- ተናገረው (Speak it/fell it) ዓውጅ ለሌላው።

በማለት ሰው በእግዚአብሔር ከመታመን በራስ ልምድና ሀሣብ መደገፍን እንዳያበዛ መንገድ ያሳያሉ።

እንደመንደርደሪያ እነዚህን ጠቀስን እንጂ በቀጣዮቹ ሶስት ምዕራፎች በጥልቀት እንመለከተዋለን።



www.ethiopianorthodox.org

## ቤተክርስቲያን ምን ታድርግ

1. በየጊዜው የመናፍቃንን እንቅስቃሴ እየተከታተሉ ለምመናን ለማሳወቅ ይጠንቀቁም ዘንድ ማድረግ "በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ትጠብቁ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጐ ለሾመበት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ" (የሐ.ሥራ 20፥28)።

2. የዘመኑን መቅረብና ምልክቱ ከሆነው አንዱ ስሙ ብዙዎች መምጣታቸውን ማወጅ፦ "ልጆቼ ሆይ መጨረሻው ሰዓት ነው የክርስቶስ ተቃዋሚ ይመጣ ዘንድ እንደሰማችሁ አሁን እንኳን ብዙዎች የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ሆነው ተነስተዋል። ስለዚህ መጨረሻው ሰዓት እንደሆነ እናውቃለን" (1ዮሐ. 2፥18)።

3. የኑፋቄ ትምህርቶች እንግዳ እንጂ የጥንት ቤተክርስቲያን ትምህርት የለመሆኑን ዘወትር ማመልከት ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ..." ዕብ. 13፥9።

4. እምነትን ማፅናት እንጂ ፍልስፍናን ያለመከተልን ማስተማር "ለውሸት እውቀት ከተባለ ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍና መከራከር እየራቅህ የተሰጠህን አደራ ጠብቅ፤ ይህ እውቀት አለን ብለው አንዳንዶች ስለ እምነት ስተዋልና" (1ጢሞ. 6፥20-22)።

ከዚህ ጋር የጠራው ትምህርቷን ለልጆቿ በአንድ አንደበትና እምነት በወንጌል መሰረትነት ማስተማር



## 1.2 ቤተ ክርስቲያንና እምነቷ

- ቤተ ክርስቲያን ማን ናት?

ቤተክርስቲያን (ኤክሌስያ) በእግዚአብሔር ሀሳብ ብቻ የነበረች በዘመኑ መጨረሻ የክርስቶስ አካልና የእግዚአብሔር ማደሪያ ቤተ መቅደስ ናት።

ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስ በደሙ የመሰረታት የምስጢራት ማከናወኛ የድኅነት ስፍራም ናት።

የቤተ ክርስቲያን ስያሜ ኤክሌሽያ ከሚለው የግሪክ ቃል የተገኘ ነው። የተጠሩ የተመረጡ የተጋበዙ ማለት ነው (1ጴጥ. 5፥13) ቤተ ክርስቲያን ብለን በኦርቶዶክሳዊ እምነት መሠረት ስንናገር የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

ሀ) ስፍራን (Place where) 1ቆሮ. 11፥18-20፤ 14፥19-35

ለ) አማኞችን (Bleavers) 2ቆሮ. 3፥15

ሐ) የክርስቲያኖችን አንድነት (Community) 1ጴጥ.513፤ ማቴ. 18፥17-18

እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው ሶስቱ ማለትም ህንፃው፣ ክርስቲያኑ፣ ማህበሩ የተሟላ የቤተክርስቲያን (ኤክሌስያ) ትርጉም ይሠጣል።

በመሆኑም በአጠቃላይ ስለቤተክርስቲያን ስንናገር

- ቤተክርስቲያን ቅድስት እንድትሆን በክርስቶስ ደም የተገዛች • ናት (1ቆሮ. 6፥19፤ የሐዋ. 20፥28)።



www.ethiopianorthodox.org

ቤተክርስቲያን በውስጧ የሚገኙ ተከታዮቿ የክርስቶስ አማኞች በመሆናቸው የቅዱሳን ሕብረት ናት (1ቆሮ. 1፥2)።

ቤተክርስቲያን አንዲት ናት (ኤፌ. 4፥4)።

ቤተክርስቲያን አግባብና ስርዓት እንዲኖራት ልዩ ልዩ መሪዎች ተሰጣት (ኤፌ. 4፥11-13)።

የምስራቹ ቃለ መናፍቲያ የወንጌል ቃል ገበታ ቤተክርስቲያን ናት፣ ለዚህም የምስራቹን ትሰብክ ዘንድ ታዛለች (ማር. 16፥15)።

ኃይል እንዲኖራት ልዩ ልዩ ስጦታ ተሰጣት (ሮሜ 12፥3-8፤ 1ቆሮ? 12፥4-11)።

ለማሰር ለመፍታትም ስልጣን አላት (ማቴ. 18፥15-20)።

ተስፋዋ የክርስቶስ ዳግም ምጽዓትና ትንሣኤ ሙታን ነው (1ቆሮ. 11፥26፤ 15፥20-22)

ቤተክርስቲያን ከላይ የተጠቀሱትን ባህርይ በመያዟ ልዩ ልዩ ጸጋ የሚገኝባቸውን ምስጢራት ታከናውናለች። እነዚህም ሰባቱ ምስጢራት (Seven Scrament) ተብለው ይጠራሉ። በዝርዝር ስናያቸው፡-

1. <u>ጥምቀት (Baptism)</u> ልጅነት የሚገኝበት ጸጋ፤ ማቴ. 28፥19፤ ማር. 16፥16፤ ዮሐ. 3፥5፤ የሐዋ.ሥራ 2፥23
2. <u>ሜሮን (Holy Oil)</u> በመንፈስ ቅዱስ የመታተም ጸጋ እምናገኝበት (1ዮሐ. 2፥10፤ 1ሳሙ.10፥1፤ ዘሌ.8፥30፤ ኢሳ. 61፥1)።
3. <u>ቅዱስ ቁርባን (Holy Eucarits Communium)</u> የዘላለም ሕይወት ምግብን የሚሰጥ ጸጋ፣ ከክርስቶስ ጋር አንድ የምንሆንበት ምስጢር (ማቴ. 27፥27፤ ማር. 10፥22፤ ሉቃ. 22፥19፤ ዮሐ. 6፥53፤ 1ቆሮ. 11፥27)።



4. <u>ንስሐ (Repentance)</u> የኃጢአትን ሥርየት የምናኝበት ጸጋ (ለካህኑ ስንናዘዝ ፍፁም ሥርየትን መፈታትን እናገኛለን።) ማቴ. 10፥4፤ ማር. 1፥44፤ ሉቃ. 5፥14፤ ሰሌ. 5፥5፤ ዮሐ.20፤ የሐዋ ሥራ 3፥19፤ ያዕ. 5፥16።
5. <u>ክህነት (Consecration or ordination)</u> የቤተክርስቲያን መሪዎችንና ምስጢራትን ሊያከናውኑ የሚችሉ የኃጢያትን ይቅር የማለት ሥልጣን ያላቸውን አገልጋዮች የምናገኝበት ፀጋ። ክህነት ደረጃው ሶስት ነው።

   ዲያቆን (Decon)

   ቄስ (Priest)

   ኤጲስ ቆጶስ (Bishop)

   ማቴ.18፥13፤ ዮሐ. 17፥20፤ የሐዋ ሥራ 14፥23፤ የሐዋ ሥራ 13፥1-5፤ 1ጢሞ. 3፥1-8፤ ቲቶ 1-5፤ ያዕ. 5፥14፤ 2ቆሮ. 2፥10

6. <u>ተክሊል (Holy marriage)</u> ጋብቻን የሚያከብርና ከሁለትነት አንድነትን የሚሰጥ፣ ጋብቻን የሚቀድስ፣ መኝታን ንፁህ የሚያደርግ ምስጢር ነው። (ዘፍ. 2፥18-25፤ ማቴ.19፥3-6፤ ዘዳ. 7፥1-4፤ 1ቆሮ 7፥39)።

7. <u>ቀንዲል (Holy Oil)</u> የሥጋ ፈውስ የሚገኝበት ለበሽተኛ ተፀልዮ የሚቀባ የፈውስ ጸጋን የሚያስገኝ ምስጢር (ያዕ.5)

እነዚህንና ሌሎች ጸጋ የሚገኝበትንም ሥርዓቶች ሁሉ እምናገኘው ቤተክርስቲያን ውስጥ ብቻ ነው። ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ድኅነት የለም እምንለው ለዚህ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

## 1.3 ቤተክርስቲያን ምን ታምናለች

### 1.3.1 ስለ እግዚአብሔር መኖር

ቤተክርስቲያን ስለእግዚአብሔር ማንነት፣ መኖር፣ መጋቢነት፣ ፈጣሪነትና ዘላለማዊ እቅዱ ቅዱስ መጽሐፍን መሰረት አድርጋ እንደሚከተለው ታምናለች፣ ታስተምራለች።

ሀ. እግዚአብሔር ማን ነው?

- እግዚአብሔር በአንድነትና በሦስትነት በዘላለማዊ መንግሥቱ ሁኖ የሚኖር እውነተኛ ህያው የሆነ አምላክ ነው።

  በባህርይው ውስን ያልሆነ የማይታዩ፣ የማይከፈል በሰው አእምሮ የማይወሰን አምላክ ነው።

  መዝ 139፡6፣ ዮሐ 4፡24፣ 1ቆሮ.8፡4፣ 1ጢ.ሞ.1፡17 ኢ.ዮ 11፡7-9 1ተሰ.1፡9 ገላ. 3፡20፣ ሮሜ. 11፡34 ዮሐ. 1፡18

- ፍጹም ቅድስና፣ ቸርነትና በጐነት የባህርይው ገንዘቡ የሆነ በምክሩ የሚሰራ፣ በደልን ኃጢአትን የሚምር፣ መተላለፍንም ይቅር የሚል፣ በፍርዱ ጻድቅና አስፈሪ፣ በደልን የሚጠላ፣ በደለኛውን ንጹህ የማይል አምላክ ነው።

  ዘፍ16፡27፣ ሮሜ.16፡27 ኢ.ሳ.6፡3፣ መዝ.115፡3 ኢ.ሳ.14፡24 ኢ.ሳ.45፡5፣ ኤፌ.1፡11 ምሳ. 6፡4 ሮሜ11፡36 ሮሜ. 1፡18፣ ዮሐ.3፡19፣ ራእይ 4፡8 ነሀ.9፡32 ዕብ.11፡6



እግዚአብሔር ሙሉና ፍፁም ክብር መልካምነትና ብፅዕነት በራሱና ከራሱ አለው። ፍጥረቶቹ (ፍጡራን) በእራሱ ህልውና አኗኗር ለውጥን አያመጡም አዲስና የሌለውን ክብርም ይጨምሩላት ዘንድ አይችሉም።
ኤር. 10፡10 ዮሐዋ. 17፡24-25 መዝ. 118፡68 ሮሜ 9፡5፤ ዮሐ 5፡26 ሉቃ. 17፡10 1ጢ.ሞ. 6፡5

እርሱ ብቻ የሕይወት ምንጭ ነው። ሁሉ ነገር ከእርሱ በእርሱ ስለእርሱ ነው። በፊቱ ሁሉ ነገር የተጋለጠና የታወቀ ነው። እውቀቱ ስህተት የሌለውና በማንም የማይደገፍና የማይታዘዝ ነው። ሁሌ ሃደቅ፣ እውነተኛ በሥራውም ትክክል ነው።

መዝ. 147፡5 ዳን. 4፡25-35 ሮሜ 11፡36 1ጢ.ሞ.6፡15 ዕብ. 4፡13 ሮሜ. 11፡33-34 የሐዋ.15፡18 ሮሜ 7፡12 ራእይ 4፡11 ሕዝ.1፡15

ለ. የእግዚአብሔር ፈጣሪነት

እግዚአብሔር የኃይሉን ክብር ጥበቡን መልካምነቱንና ፍቅሩን ለመግለፅ የማይታዩትንና የሚታዩትን 22 ስነፍጥረታት ሁሉ በስድስት ቀን ፈጠረ የፈጠረው ሁሉ መልካም ነበር።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘፍ- 1፡12 | ኤር. 10፡12 | ዕብ. 1፡2 | ኢ.ዮ. 33፡4 |
| ዮሐዋ. 17፡24 | ሮሜ. 1፡20 | መዝ. 33፡5 | ዘጸ.20፡11 |
| ሮሜ 11፡36 | መዝ.104፡24 | ዕብ.11፡3 | ዘጸ. 20፡11 |

ሌሎች ፍጥረታትን ከፈጠረ በኋላ ሰውን ወንድና ሴት አድርጐ ፈጠረ ሕያውነትና፣ ነባቢነት ለባዊነት ካላት ነፍስ ጋር መሬትነት እሳትነት ነፍሳትንና ውሃነት ያላትን ሥጋ አዋህዶ በራሱ መልክና ምሳሌ ሰውን



www.ethiopianorthodox.org

ፈጠረው። ሰው በሌሎች ፍጥረታት ላይ ሲጨመር የእግዚአብሔር ሥራ እጅግ መልካም ነበር።

ዘፍ. 1፥27፣ ሉቃ. 23፥24 መዝ. 8፥6-8 ዘፍ.2፥7፣ ማቴ.10፥28፣ መክ.12፥7፣ ቆላ.3፥10፣ ዘፍ.1፥20፣ ኤፌ..4፥24፣ ዘፍ.3፥6 ሮሜ 2፥14-15

መልካሙንና ክፉውን የምታስታውቀውን ዛፍ እንዳይበላ ለሰው ትዕዛዝን ሰጠው። ትዕዛዙ የፍጡርና የፈጣሪ፣ የአባትና የልጅ፣ የጌታና የአገልጋይ መለያ የመታዘዝም ምልክት ነበር። ሰው ይህንን ትዕዛዝ እስከጠበቀበት ቀን ድረስ ከፈጣሪው ጋር በሰላም ይኖር ነበር። ኃጢአትን በሠራ ጊዜ ግን ወደቀ።

ዘፍ. 3፥18-17፣ ሕዝ. 8፥6-8 ዘፍ. 2፥17

## ሐ. <u>መግቦተ እግዚአብሔር</u>

መጋቤ አለማት እግዚአብሔር ፍጥረታትን ሁሉ ከታላቁ እስከ ታናሹ በማይናወጠውና በማይለወጠው በማያልፍ መንግሥቱ በፍቅሩና በቸርነቱ መግባል።

ነህ 9፥6 መዝ.145፥14-16 ዕብ.1፥3 መዝ.135፥6 ሥራ. 17፥25-28 ኢዮ.38፥1-41 ማቴ.10፥29 ማቴ. 6፥26-32 ምሳ. 15፥3 2ዜና 16፥9 ኢሳ. 42፥9 ሥራ. 15፥18

ሁሉን ነገር እግዚአብሔር ባለመለወጥና ያለስህተት ይፈፅማል በፍጡሩ አድሮ ወይም አማካኝነት ይሠራል ያለፍጡሩም እንደወደደ ያደርጋል። የማይመረመረውና ወሰን የሌለው ፍቅሩ ዓለምን በሚገዛው መንግሥቱ ሁሌ ይገለጣል። የሰው ልጅ በኃጢያት በወደቀ ጊዜ የዓመፅ ሥራውም በበረታ ሰዓት ሁሉ <u>መግቦቱ አልተቋረጠም</u>።



የሰው ልጅም የመረጠውንና የወደደውን ያደርግ ዘንድ የተሟላውን ነፃ ፈቃሉ (freewill) ከመጋቢ ዓለማት ከእግዚአብሔር ተቀበለ። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር የክፋትና የአመፅ ምንጭ አልነበረም። የተቀደሰውና ፍፁም የሆነው ባሕርይው የኃጢአት መነሻ ወይም የኃጢአት ደጋፊ አይሆንም። ነገር ግን በነፃ ፈቃድ የተፈጠረው ሰው ከአምላኩ ትዕዛዝ ሲወጣ ክፋትና ስህተት መጠበት ይበዛም የመተላለፍ ውጤቱ ነው።

ኢሳ. 55፥10-11 የሐዋ. 2፥23 ኢሳ..45፥7 ዘፍ.8፥22 ኢሳ.14፥24-27 2ሳሙ. 16፥10 መዝ.50፥21 ኢር. 31፥35 ሮሜ 11፥32 የሐዋ. 27፥24-31 ሆሴ.1፥7

## 3.1.2 <u>ስለሥላሴ የቤተክርስቲያን እምነት (Trinity)</u>

ቤተ ክርስቲያን የምስጢረ ሥላሴ ትምህርቷን እምታምነው በአንድ መለኮት ሶስት አካላት አሉ፤ ሶስትነታቸውን በስም፣ በአካል፣ በግብር ነው። በስም አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ይባላሉ። በግብር ወላዲ፣ ተወላዲ፣ ሰራፂ ይባላሉ። የአብ ግብሩ መውለድ ማስረፅ፣ የወልድ መወለድ፣ የመንፈስ ቅዱስ መስረፅ ናቸው። ይህ የአካል ግብር የአካል ከዊን (መሆን) ይባላል ብላ ታምናለች፣ ታስተምራለችም። መሰረቷም ቅዱስ መጽሐፍ ነው።

እነዚህ ሶስት አካላት (ሥላሴ) ሦስት ገፃት፣ አንድነታቸው በባህርዩ፣ በሕልውና፣ በፈቃድ እንዲሁም በመለኮት ነው። መበላለጥ፣ መቀዳደም በሥላሴ የለም። አንዱ ከአንዱ ተለይቶ የነበረበት ዘመን የለም። በሕገ ተፈጥሮ አባት ልጁን እንደሚቀድም በሥላሴ ግን ይህ የለም፤ አብ ወልድን ቢወልድ፣ መንፈስ ቅዱስን ቢያሰርፅ አይቀድምም፤ አይበልጥምም። ይህ ምስጢር ይደነቃል እንጂ አይመረመርም መባሉ ለዚህ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

ምክንያቱም የእግዚአብሔር ሕልውና ከተፈጥሮ ሕግ ውጭና ከሰው አእምሮ በላይ ነውና።

በምስጢረ ሥላሴ ተተንትኖ የቀረበው በሶስት አካላት የማመን ትምህርት በብዙ አማልክት እንደሚያምኑ አህዛብ አያስኝም። ቤተክርስቲያን ስለአንድነት ስታስተምር ሦስትነትን አጣፍታ፤ አንድ ገፅ ብቻ አትልም፤ ስለ ሶስትነት ሥታስተምር አንድነትን አጣፍታ ሦስት አማልክት አትልም፤ ነገር ግን አንድነትን በሶስትነት ሶስትነትን በአንድነት ታስተምራለች እንጂ።

ዘፍ.1፥26 መዝ.138፥7-10 ማቴ.3፥16-17 ዘፍ.3፥22 ዘጸ.17፥7 ማቴ. 28/፥19 ዘፍ. 11፥6-7 ኢሳ. 6፥6 ዮሐ.14፥9 ዘፍ. 18፥1-15 ኢሳ.53፥1 ዮሐ. 15፥26 ዘዳ. 6፥4-5 ኢሳ. 51፥91ቆሮ. 13፥16 መዝ. 2፥9 ዮሐ. 5፥9

## 1.3 የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ

ቤተ ክርስቲያን ስለጌታ ኢየሱስ የምታስተምረው ትምህርት ፍጹም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። ኢየሱስ ማለት መድኃኒት፣ ክርስቶስ ማለት መሲህ ማለት ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ አምላክ ነው። ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በባህርይ ትክክል የሆነ ሁሉ በእርሱ የሆነ ከሆነው ያለእርሱ አንዳች የሌለ ከኃጢአት በስተቀር ሙሉ የሰውን ባህርይ የተዋሀደ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባህርይ አንድ ባህርይ ሆነ። ማለትም በተአቅቦ ፍጹም ሰው፣ ፍጹም አምላክ ሆነ።



ዮሐ. 1፥1-4 ፊል. 2፥6 ገላ.4፥4 1ዮሐ. 5፥10 ዕብ. 2፥14-16 ሉቃ.1፥27-31 1ጢሞ. 2፥5 ማቴ. 1፥18-20 ማቴ. 16፥16 ቆላ. 2፥9 ፊል. 2፥7

የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ የጠፋውን ሊፈልግ፣ በጨለማ ላለው ብርሃን ሊሆን፣ ለተራበው የሕይወት ምግብ ለተጠማው የሕይወት ውሃ ሊሆን ለታሰሩት መፈታትን፣ ለተጠቁት ነፃነትን ለዕውራን ማየትን ይሰጥ ዘንድ የሰው ፍቅር አገብሮት በመልአክ ብስራት በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከአንስተ አለም መርጦ በንፅህናና በድንግልና ተጠብቃ በኖረች ከእመቤታችን ድንግል ማርያም በማህፀኗ አደረ። ተወለደ እንደ ሕፃንም አደገ።

- በሥጋ በመገለጡም የተጐዳውንና የተጠቃውን የሰውን ልጅ ነፃ ያወጣ ዘንድ ከሕግ በታች ሆነ፣ ሕግንም ፈፀመ በሥጋው ወራትም በተዓምራቱ ህሙማን ሥጋን፣ በቃሉ ህሙማን ነፍስን እየፈወሰ ለ3 ዓመት ከሶስት ወር አስተማረ፣ ሙት አስነሳ፣ ልዩ ልዩ ተአምራትን አደረገ። ደቀ መዛሙርቱን መርጦ ለአገልግሎትም አዘጋጃቸው። የሰውል ልጅ (ወልደ እጓለምሕያው) እንደተፃፈለት ይኖራል ብሎ አስተማረ በነቢያት ተነገረው ትንቢት እንደሚፈፀም ሲያመለክት። በዚህም መከራን ተቀበለ፤ ተሰቃየ፣ ሞተ፣ ተቀበረ፣ መበስበስን (ሙስናን) ሳያይ የሞትን መውግያ ሰበረ። ከሙታንም በሶስተኛው ቀን በለበሰው ሥጋ ተነሳ፤ ለሐዋርያቱም ታየ፣ ወደሰማይም በለበሰው ሥጋ አረገ፣ በአባቱ ቀኝ ተቀመጠ፣ ዳግም ለፍርድ በግርማ መንግሥቱ በክበበ ትስብዕቱ (በሥጋ) ተመልሶ ይመጣል።

መዝ. 40፥7-8 ዕብ. 5፥8-9 ዕብ. 10-5-10 ማቴ. 26፥37-38 ዮሐ.4፥34 ማቴ.27፥27-50 ማቴ.3፥15 ማቴ.26፥60 ሉቃ.3፥15 ሮሜ.14፥10 የሐዋ.20፥24-27 ሮሜ 6፥9 ማር.15፥24-37 ሥራ.1፥11 ሥራ.10፥42 ሥራ.7፥1-9



www.ethiopianorthodox.org

ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር በኖረ ዘመን በነቢያት የተነገረለትን የነቢይነት፣ የንጉሥነትና የካህንነት ሥራውን አከናውኗል።

## ሀ) <u>ነቢይነት፡-</u>

ሙሴ ስለሚመጣው ነቢይ የተናገረውን ክርስቶስ ፈፀመው (ዘዳግ. 18፥15-19፤ የሐዋ. ሥራ 3፥22) እንደ ነቢይም የሚመጣውን ገለጠ፣ የእግዚአብሔርን ሕግ ተረጐመ፣ ሰዎችን ስለኃጢያታቸው ወቀሰ፣ ስለእምነታቸውም አበረታቸው።

ሉቃ 19፥41-44 ማቴ.5-21-48 ሉቃ.11፥42-44 ማቴ. 8፥10-13

## ለ) <u>ካህንነት፡-</u>

ኢየሱስ ክርስቶስ ከአሮን ወገን ያይደለ እንደ መልከጼዴቅ ያለ ካህን እንደሚነሳ የተተነበየውን ፈፀመ። መልከጼዴቅ ክህነቱ ከአሮን ክህነት ይበልጣል። ለዚህም ሁለት ምክንያቶች አሉ።

1. በሥጋዊ ትውልድ ሳይሆን በእግዚአብሔር መሐላ በመሾሙ (ዕብ. 5፥5፤ 6፥7፤ 7፥13-15)
2. በሞት ሳይወሰን ለዘላለም በማገልገሉ (ዕብ. 6፥20፤ ገላ.3፥23-25)

ኢየሱስ እንደመልከጼዴቅ ያለ ካህን በመሆኑ የአሮንን ክህነት አስቀርቷል።

ካህን ሁለት መሠረታዊ ሥራዎችን ይሰራል፡-

ሀ) መስዋዕት ማቅረብ፣

ለ) መጸለይ (በእግዚአብሔር ፊት መቆም) ናቸው።



ኢየሱስ እነዚህን ነገሮች አከናውኗል።

### <u>መስዋዕት፡-</u>

ኢየሱስ እራሱን የተወደደ መስዋዕት አድርጐ አቀረበ በዚህም የአሪቱን መስዋዕትና የሊቀካህናቱን ሥራ ፈፀመ። እራሱ መስዋዕት እራሱ መስዋዕት አቅራቢ ተቀባይም ሆነ የአዲስ ኪዳን በግ ስለሆነ ነዋ በግዑ ተብሎ ተነገረለት። ሞቱ ቤዛነት ማስተስረያ መስዋዕት ነውና።

ሁለተኛው የካህን ተግባር መጸለይ ነው። በጸሎቱ ሰውንና እግዚአብሔር ይገናኛል። ክርስቶስ በምድር ሳለ ሕዝቡን ከእግዚአብሔር አባቱ ጋር መንገድ ሆኖ አገናኘ። በልጁ ለማያምኑ የእግዚአብሔ ልጅ እንዲባሉም ሥልጣንን ሰጣቸው። አባ ስረይ ሎሞ ብሎ ጸለየ፣ ጸሎትንም አስተማረን። አሁን በአባቱ ቀኝ ስለሁሉም ይፈርዳል። አዳኝ ሆኖም ይኖራል።

ዮሐ. 1፥29 ሮሜ. 3፥26፤ 5፥6 ኢሳ. 53፥5-6 ማር.10፥25
1ጴጥ.2፥24፤ 3፥18 ራእ ፐ፥4-5 ሉቃ. 22፥32 ዮሐ. 17፥፥6-26

## ሐ. <u>ንጉሥነት፡-</u>

ኢየሱስ ከዳዊት ቤት ለዘለዓለም ንጉሥ እንዳይጠፋ የተሰጠውን ተስፋ ፈፀመ። ንጉሥ ሰማይ ወምድር ነው፤ የቤተክርስቲያን ራስ ነው። ንጉሥ በመሆኑ መንግሥቱ የማያልፍ ዘለዓለማዊና ሰማያዊ ነው። በንግሥናውም ለዓለም ፍፃሜ ለፍርድ ይመጣል፤ ይፈርድማል።

2ሳሙ.7፥12-16 ራእይ 22፥16 ማር.28፥18 ሉቃ.1፥33 ዮሐ.18፥36 ራእይ 11፥15



www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ ቤተክርስቲያን የእምነቷ መሰረት፣ ጉልላትም እርሱ ነው። ስሙን ጠርታ አጋንትን ትገስፃለች፣ እምነትን፣ ትጠብቃለች፣ ከምድር በላይ ከሰማይ በታችም ከስሙ ውጭ አዳኝ እንደሌለ ታምናለች። በመሆኑም፦

- መድህንን
- ጌታ
- ቸር እረኛ
- የቤተ-ክርስቲያን ሙሽራ
- ሕይወት
- ብርሃን

እያለች ስሙን እየጠራች ታመሰግነዋለች። አማኞቿም ስለፍቅሩ በእሳት ይጣላሉ በሰይፍ ይታረዳሉ። በአላውያን ይጨቆናሉ። ነገር ግን በዚህ ሁሉ "ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለይናል እያሉ ይዘምራሉ፣ ይመሰክራሉ።"

## 1.4 የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ስለመንፈስ ቅዱስ

ቤተ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ ከሶስቱ አካላት አንዱ አካል መሆኑን በቅዱስ መጽሐፍ መሰረት ታምናለች።

የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት የሚክዱ ብዙ መናፍቃን አሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ለሚኖር ሁሉ ግን ስለመንፈስ ቅዱስ የሚከተለውን ያውቅ ዘንድ ይገባል።

- መንፈስ ቅዱስ መለኮታዊ ባህርያት አሉት። መለኮታዊ ባህርይ ማለት ከአምላክ ብቻ በቀር ማንም ፍጡር የሌለው በህርይ ማለት ነው። ከእነዚህ ባህርይ መካከል።
- ዘላለማዊ ነው ዕብ. 9፥14
- በሁሉ ቦታ ይገኛል መዝ. 139፥7-10



- ፈጣሪ ነው ኢዮ. 33፥4
- ከአብ ከወልድ ጋር በአንድነት ሶስተኛ አካል ሆኖ ተጠርቷል ማቴ. 28፥19
- ሁሉን ያውቃል 1ቆሮ. 2፥11
- ቤተክርስቲያን ከበዓለ ሀምሳ ቀን ጀምሮ የምትመራው በመንፈስ ቅዱስ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ስትመራም ሀይልንና ቅድስናን ጭምር የሚሰጣት። በዚህም መሠራት።
- የፀጋ ስጦታን ይሰጣል ሮሜ. 1፥11 1ቆሮ.12፥4 1ጴጥ.4፥10
- ምዕመናን ዳግም እንዲወለዱ በጥምቀት ግዜ ያደርጋል ዮሐ. 3፥3-7 ቲቶ. 3፥5
- የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ይሾማል። ሥራ.13፥2-4 እና 16፥6-10
- በቤተ ክርስቲያን ውሳኔ (ሲኖዶስ) አብሮ ይወስናል የሐዋ. 15፥28
- እያንዳንዱ ምስጢራት በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ይለወጣል ይከናወናል። ኤፌ. 2፥19-22

## 1.5 ስለ ሰው ተፈጥሮ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት

የሰውን ተፈጥሮ ቤተክርስቲያን ቅዱስ መጽሐፍን መሰረት አድርጋ የሚከተለውን ታስተምራለች።

ሰው በእግዚአብሔር አርአያ የተፈጠረ ነው። ሕያዊት ነፍስና የሚሞት ሥጋን ይዟል። ነፍስና ሥጋ በሞት በሚለያዩበት ጊዜ ሥጋ ወደ መቃብር ይወርዳል ነፍስ ደግሞ ሕያዊት በመሆኗ እንደ ሥራዋ በዘላለም ስቃይና በዘላለም ሕይወት ትኖራለች።



www.ethiopianorthodox.org

## የሰው ውድቀት

የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን አዳምና ሔዋን በሰይጣን ተንኮል ፈተና አትብሉ የተባሉትን በመብላታቸው ኃጢያትን ሰሩ። በመተላለፋቸውም የመተላለፍ ውጤት ህይወታቸውን ይገዛ ጀመር።

በኃጢያት ምክንያት የነበራቸው ፀጋ ተገፈፈ ባህርያቸውም ጐሰቆለ፣ ከአምላካቸው ጋር የነበረው ዝምድና ተቋረጠ በኃጢያት ሞት፡ በነፍሳቸውና በሥጋናቸው በኃጢአት ረከሰ።

ሮሜ. 5፥12 ዘፍ. 3፥6-8 ሮሜ.3፥23 ኤር.17፥9
ዘፍ- 2፥17 ኤፌ. 2፥1-3 ቲቶ. 1፥15 ዘፍ.6፥5

በእነሱ ምክንያት በልጆቻቸው ሁሉ ተፈረደ ፍርዱም የኃጢያትና የሞት ፍርድ ነበር። በዚህም ምክንያት የሰው ልጅ ሊያመልጥ ከማይችለው። ርኩሰት ለመንፈሳዊ ሥራ ሙት የሆነ መንፈስ ውስጥ ገባ። ከባህርዩው ኃጢያትን እያመነጨ ምድርን በኃጢያት አሳደፈ። አረከሰም እግዚአብሔርን ፍጡርን በመፍጠሩም አዘነ።

ዘፍ. 5፥6 መዝ. 51፥5 ዮሐ. 17፥26 ያዕ. 1፥14-15
ዘፍ- 8፥21 ማቴ. 15፥19 1ቆሮ. 15፥21-22 ቆላ.1፥21
ሮሜ.5፥12 ሮሜ. 5፥6 ዮሐ. 3፥6 ኢዮ. 15፥14 ኤፌ. 2፥2-3

የእግዚአብሔርን ሕግ መተላለፉ ኃጢያትን ማድረግ ስለሆነ ኃጢአተኛው ለእግዚአብሔር ቁጣና ለሕጉ ርግማን የተመደበ ሆነ ለመንፈሳዊ፣ ለነፍስና ለሥጋም ሞት ተገዥ ሆነ።



በዚህ ሕይወት ውስጥ የነበረ ሰው መዳንን ሽቶ ለመነ፣ ጮኸ ተጣራ የወገኖቹን መከራ ጩኸትም የሰማና የተመለከተ እግዚአብሔር ልጁን ልኮ ወሰን በሌለው ፍቅሩ በመስቀል ሞት አለምን ወደደ አዳነውም፤ የጐሰቆለውን የሰውን ባሕሪ አደሰው።

ማቴ.25፥41 1ዮሐ.3፥4 ሮሜ. 6፥23 2ተሰ.1፥9
ሮሜ. 2፥15 ኤፌ.4፥18 ዘጸ.3፥15 ኤፌ.2፥3
ሮሜ. 8፥28 ገላ. 3፥10 ሰቆ.ኤር. 3፥39 ገላ. 4፥4

## 1.6 ድኅነት በቤተ ክርስቲያን ትምህርት (Salivation)

በቤተክርስቲያን እምነት ብቸኛው የድኅነት ምንጭ በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመንና እምነቱን እንደ ቤተክርስቲያን ስርዓት በግብር መግለጥ መሆኑን ታስተምራለች።

ወልድ ያለው ሕይወት አለው በማለት ቅዱስ መጽሐፍ ባስተማረው መሠረት የመዳናችን መሠረት እርሱ ብቻ ነው። ይህንን የመዳን ትምህርት ቤተክርስቲያን በእራሷ ቀኖና እና ዶግማ ዝግጅት መሠረት ሰው ለመዳን ፀጋን ሊሠጡና መዳኑን ሊያረጋግጡ በሚችሉ ሥርዓት ውስጥ ማለፍ እንዳለበት ታስተምራለች። ስለዚህ በትምህርቷ መሠረት ያመነው ሰው ሃይማኖቱን ይመሰክራል፣ በሥላሴ ስም ይጠመቃል፣ ሥጋውና ደሙንም ከመቀበል ጋር በሜሮን ይታተማል።

ድኅነትን ያገኘ ክርስቲያን ለመዳኑ የእሱ ጥረትና ሥራ ውጤት ሳይሆን በጸጋው መሆኑን ይገነዘብ ዘንድ ይገባልዋ።

ሮሜ11፥12-17 የሐዋ ሥራ 17፥31 1ጢሞ.2፥5 ዮሐ.3፥16
ዮሐ.17፥6 ዮሐ. 6 ኤፌ. 5-23 ዕብ.5፥5-6 ማቴ. 28፥19



www.ethiopianorthodox.org

በአዲስ ኪዳን መዳን የተጠቀሰ ብዙ ክፍሎች አሉ። ይሁንና ድኅነት አብዛኛው ጊዜ የሚያመለክተው አዲስ ሕይወትን መኖርና ከኃጢያት መንጻት ነው። ይህም አስቀድመን እንደተመለከትነው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው (ዮሐ. 3፥16)። የክርስቶስ ስለእኛ መተላለፍ ሞቱ፡ ትንሳኤው ድኅነትን አመጣልን ሮሜ. 4፥24-25፤ ኤፌ. 2፥13-18።

መዳንም ስንናገር እንደ ቤተክርስቲያን ትምህርት ከሚመጣው ፍርድ ለመዳን ብቻ ሳይሆን በሕይወት (ሥጋ ዘመን) ሳሉም ከኃጢያት ኃይል እስራት ነፃ መውጣት መሆኑን አጥብቀን ልናውቅ ይገባናል። የዳነ አማኝ ኃጢያት አይነግስበትምና ሮሜ6 ይመልከቱ።

በክርስቶስ የሚያምን ድኅነትን ያገኛል ስንል የሚከተሉት በረከቶች ከእርሱ ጋር ይሆናሉ። እነርሱም፦

- የእግዚአብሔር ልጅ መሆን (ዮሐ. 1፥12)፣
- ከአዳማዊ ኃጢያት ነፃ መሆን (ገላ. 5፥1፤ ሮሜ 6፥2 ገላ. 5፥24)
- በክርስቶስ ለክርስቶስ መለየት (ቲቶ 2፥14)፣
- መክበር፣ (ሮሜ. 8፥30)
- መቀደስ (1ቆሮ. 6፥11)
- መንግሥቱን መውረስ፣ የጽድቅንም አክሊል በመቀዳጀት ለዘላለም በሕይወት ይኖራል (ፊሊ. 1፥6፤ 2ጢሞ. 1፥12፤ ዮሐ. 10፥27-28፤ ማቴ. 24፥13፣ 2ጢሞ. 4፥8)።



## 1.7 ስለ አስቀድሞ መወሰን /Per-distination/ የቤተክርስቲያን እምነት

ቤተክርስቲያን ስለአስቀድሞ መወሰን ወይም መመረጥ የሚከተለውን ታምናለች። የክርስቶስ ወደምድር መምጣትና ሥጋ መልበሱ፣ በመስቀል የመሞቱ አላማው የሰውን ዘር ሁሉ ለማዳን ነው። "መመረጥና አስቀድሞ መወሰን" የሚለው ቃል የሚያመለክተው የሰውን ዘር ሁሉ እንጂ የተወሰኑ ሰዎችን አይደለም። በቅዱስ ቃሉ መሠረት እግዚአብሔር ይጣራል፣ ይፈልጋል፣ ለጥሪው መልስ መስጠት፣ በፍላጋው ውስጥም ለመገኘት ፈቃደኛ መሆን በነፃነት (Free will) የተፈጠረው የሰው ፈንታ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልጁ ሞት በኩል የተገለጠው ለተወሰነና ለተመረጠ ሰው ብቻ አለመሆኑን ሲገልጥልን "እግዚአብሔር አንድያ ልጁን አሳልፎ ለሞት እስኪሰጥ ድረስ <u>ዓለሙን እንዲህ ወዶታል።"</u> ዮሐ. 3፥16 ይላል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም የአህዛብን መመረጥና መጠራት አስመልክቶ የእግዚአብሔር መንግሥት ተስፋ ላልተነገረለት ህዝብ ለአህዛብ መስጠቱን ተናግሯል። ሮሜ. 11፥12-17፣ የሐዋ 17፥31፣ ዮሐ. 3፥16፣ ዕብ. 5፥5-6፣ 1ጢሞ. 2፥5።



www.ethiopianorthodox.org

## 1.8 ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር ስለመረጣቸውና ስላከበራችው ቅዱሳን መላዕክትና ሰዎች የሚከተለውን ታስተምራለች።

### ሀ. ስለድንግል ማርያም (St. Virgen Mary)

ቤተክርስቲያን ስለድንግል ማርያም ክብርና ምስጋናን ስታቀርብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት አላት። በዚህም መሠረት ስለድንግል ማርያም የሚከተለውን መሠረታዊ እምነት ታስተምራለች።

- ሰው ከሆኑ ከእያቄምና ሐና መወለዷን ታምናለች (ሉቃ.1፥3፣ ማቴ.1፥1)።
- ዘላለማዊ ድንግል መሆኗን ታምናለች ይህም ከመፀነስ፣ ሀንሳ፣ ከፀነሰች በኋላ ከሳትወልደው በወለደች እንዲሁም ከወለደችው በኋላ ድንግል ናት። (ሕዝ. 44፥1፣ መኃልይ 4፥12፣ ዮሐ.19፥26፣ ማቴ. 1፥18፣ ኢሳ. 7፥14፣ ሉቃ. 1፥26-28)።
- ወላዲተ አምላክ (ኢሳ.7፥14፣ ሉቃ.1፥43፣ ዮሐ.1፥14፣ ገላ.4፥4)።
- በጌታ ፊት በምልጃ ትቆማለች (ዮሐ.2፥1-11፣ ዮሐ.19፥26፣ ሉቃ.1፥48፣)
- ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል ብላ እንደተናገረች ቤተክርስቲያን የምስጋናዋን ስርዓት ሰርታ ታመሰግናታለች። በምስጋናውም ሥርዓት አበው ቅዱሳን ያዘጋጁትን ድርሰቶች አጥብቃ ትጠቀምበታለች። የቅ.ኤፍሬም ውዳሴ የአባ ሕርያቆስ ቅዳሴ የቅዱስ ያሬድና የሌሎች ሊቃውንት ምስጋና ናቸው። (በሐዲስ ሉቃ.1፥28፣ ሉቃ.1፥41፣ ሉቃ.1፥47-53፤ በብሉይ መዝ.44፥9-12፣ መዝ.44፥14፣ መዝ.132፥13፣ ኢሳ.11፥1)።



- እነዚህ ቤተክርስቲያን ስለእመቤታችን ከምታስተምረው አጭሩ ነገር ግን መሠረታዊ የሆነው እምነቷ ነው።

### ለ. ስለሞቱ የእግዚአብሔር (ቅዱሳን) ሰዎች (Saints)

ቤተክርስቲያን የሰውን ተፈጥሮ ስታስተምር የነፍስን ሕያዊነትና ዘላለማዊነት አጥብቃ ታስተምራለች። በዚህ መሠረት የሞቱ ቅዱሳን ሰዎች በዘላለማዊ ኑሮ ውስጥ ስላሉና አምላካቸውም የሕያዋን አባትና አምላክ በመሆኑ ምድራዊ ኑሮ ሲጨርሱ አረፉ እንላቸዋለን፡ ቤተክርስቲያን በእነዚህ ቅዱሳን ያላትን አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርጋ የሚከተለውን ታስተምራለች።

- የሞቱ ቅዱሳን ሕያዋን መሆናቸውን፣
- በምድር የነበራቸው የማስታረቅና የማማለድ ሥራ በሰማያትም እንደሚከተላቸው (2ነገ.13፥2፣ 1ነገ13፥31፣ ማቴ.10፥41፣ ራእይ 6፥9)።
- በስሙ ድንቅ ሊያደርጉ በምድር እንደቻሉ ስለእነሱ እንዲምር በስማቸው መለመን (መጸለይ፣ መማለድ) እንደሚገባ ታምናለች። (ማቴ. 8፥5፣ ማቴ. 17፥14፣ ማቴ. 9፥5፣ የሐዋ 9፥36፣ ማቴ. 15፥32፣ ያዕ. 5፥ ይመልከቱ)
- በስማቸው ለመታሰቢያ የቤተክርስቲያን መሰየም ኢሳ. 56፥
- የተቀደሰውን የእምነት ሥራቸውን ተመልክተው ሰዎች ለክርስቶስ እንዲገዙ የመታሰቢያቸውን በዓል ማድረግ ወዘተ



www.ethiopianorthodox.org

### ሐ. መላእክት (Holy Angles)

ቤተ ክርስቲያን ስለ ቅዱሳን መላዕክት እምነቷ እንደሚከተለው ነው።

- እሳታውያን ረቂቃን ፍጥረታት ናቸው (መዝ. 103፥4)
- ለበረከትና ለቅጣት (ለመቅሰፍት) ከጌታ ዘንድ ይላካሉ (መሳ. 13፥ ዳን. 9 ሉቃ. 1፣ ዘካ. 4፣ ዘፍ. 19፣ 2ነገ. 19፥35)።
- ተቀዳሚ ሥራቸው የሆነውን ምስጋና ለእግዚአብሔር ዘወትር ያቀርባሉ (ኢሳ. 6፥3፣ ራእይ 7፥7)።
- የእግዚአብሔርን ምህረት ወደሰው የሰውን ፀሎት ወደእግዚአብሔር ያቀርባሉ (ዘካ.1፥12፣ ራእይ 8፥5፣ ራእይ 5፣)።
- መላእክት አይገቡም አይጋቡም ቁጥራቸውም ብዙ የብዙ ብዙ ሲሆን አይወሰንም (ሉቃ. 24፥39፣ ማቴ. 22፥30)።
- ከመላዕክት ወገን ሰውን ለማዳን ሥጋ የለበሰና የተገለጠ የለም። ዕብ.4፥10

## 1.9 ቅዱስ መጽሐፍ (HOLY BIBLE)

ቤተክርስቲያን ስለቅዱስ መጽሐፍ የሚከተለውን ታስተምራለች።

- ቅዱሳት መጻሕፍት የእምነትና የሕይወት መመሪያ ይሆኑ ዘንድ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተፃፉ ናቸው። (ሉቃ. 16፥29-31፣ ዮሐ. 5፥40-47፣ 2ጢ.ሞ. 3፥15-16)።



- መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ኃይል ጥበብና በጎነት እንዲሁም መለኮታዊ ሕልውና የሚያውጅ ነው። (ሮሜ. 2፥14-15፣ መዝ. 19፥1-4፣ ሮሜ 1፥32፣ ሮሜ. 2፥1)።
- እግዚአብሔር በልዩ ልዩ ዘመናት በልዩ መንገዶች እራሱን የገለጠበትን መንገድ ሊገልፅና ፈቃዱን ለልጆቹ ሊያውጅ በመንፈስ ቅዱስ የተመራ መጽሐፍን እንዲሰራ አደረገ (ሉቃ.1፥3-4፣ ሮሜ 15፥4፣ ማቴ.4፥4፤ 7፥10፣ ኢሳ.8፥20፣ ዕብ. 1፥1-2)።
- ልናምነው ልንታዘዘው የሚገባን የመጽሐፍ ቅዱስ ስልጣን የተመረኮዘው <u>በማንም ሰው</u> ወይም <u>ድርጅት ምስክርነት</u> ላይ አይደለም። ነገር ግን እውነት በሆነውና ደራሲው በእግዚአብሔር ላይ ነው። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ብቻ መሆኑን ሊታመን ይገባል። (2ጢ.ሞ. 3፥15-16፣ ዮሐ. 5፥40-47)።
- መጽሐፍ ቅዱስ ፍጹም ስህተት አልባ ነው። ይህንንም የምናምነው በአፃፃፉ፣ በታሪክ አደራደሩ፣ በቃላት አሰካኩ ወዘተ ብቻ ሳይሆን ከቃሉ ጋር በመተባበር በልባችን ውስጥ ከሚመሰክረው ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሥራ የተነሳ ነው። (1ቆሮ.2፥9-10፣ ዕብ.4፥12፣ ዮሐ.10፥35፣ ኢሳ.55፥11፣ ሮሜ 11፥36፣ 1ዮሐ.2፥20-22፣ መዝ.19፥7-11፣ 2ጢ.ሞ.3፥15፣ 1ተስ1፥5)።
- መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ክብርና ስለሰው ደኅንነት ስለ እምነትና ስለ ኑሮ በግልፅ ተፅፎበታል። የእግዚአብሔር ሃሣብም ነው። ነገር ግን ሰዎች ለትውልድ የሚመች ወገንና ልፍለፋን ተረትንም እንዲሁም አዲስ መገለጥ ብለው ይጨምሩበት ዘንድ አይችሉም (ራእይ 22 2ጢ.ሞ. 3፥15-17፣ ገላ. 1፥8-9፣ 2ተሰ. 2፥2፣ ገላ. 3)



www.ethiopianorthodox.org

- ቤተክርስቲያን ሥርዓትን፣ ቀኖናን ወዘተ የመሳሰለና እንዲሁም አስተዳደር ነክን (ፍትህ መንፈሳዊ) በተመለከተ በግልፅ ያልተቀመጠ ከሆነ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ሐዋርያትን መስለው የተነሱ አባቶቻችን ሊቃውንት የሰሩትንና በትውፊት የደረሰውን መቀበል ተገቢ ሲሆን፤ ነገር ግን ሁሉም በቃሉ ሚዛንነት ሊመረመሩ ይገባል። (1ቆሮ. 11፥13-14፣ 1ቆሮ. 14፥26-40)።
- በሃይማኖት ድንጋጌዎች፣ ክርክሮች፣ መናፍቃንን ለመርታት፣ ቤተክርስቲያን የመጨረሻ አቤቱታዊ ማስረጃና ምስክር አድርጋ ቅዱስ መጽሐፍን ታቀርባለች (ኢሳ. 8፥20፣ ማቴ. 15፥3-6፣ ሉቃ. 16፥31፣ ዮሐ. 15፥15)።

እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው ስለቅዱስ መጽሐፍ መሠረታዊ ቤተክርስቲያን ትምህርቶች ሲሆኑ በዚህ መሠረት ላይ ያለች ቤተክርስቲያን 81 መጽሐፍ ቅዱሳትን ትቀበላለች ይኸውም 35 የሃዲስ ኪዳን፣ 46 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ናቸው። ከሰላሳ አመስቱ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት 8ቱ የስርዓት መፃሕፍት ሲሆኑ ለአምልኮትና ለስርዓተ ቤተክርስቲያን መገልገያነት ተጠቅማበታለች። ከዚህ በተጨማሪ በትውፊት ደረሱትን ልዩ ልዩ ድርሳናት፣ ገድል፣ ተዓምራት ወዘተ እንዲሁም የሊቃውንት ትምህርት በቃሉ እየመዘነች ትቀበላቸዋለች።

## ማጠቃለያ

ከላይ በመጠኑ የተመለከትነው እጅግ ጥልቅና ረቂቅ የሆነውን የቤተክርስቲያን እምነትና ትምህርቷን በዚህች ቁንፅል ጽሁፍ



የመመልከታችን መሠረታዊ መልእክት መናፍቃን በእነዚህ የክርስትና ትምህርት ላይ የሚሰጡትን የክህደትና ኑፋቄ ቃል በጠለቀ መልኩ እንድናነፃፅረው ስለሚረዳ ነው። ቤተክርስቲያን እጅግ ሰፊና ጥልቀት ያላቸው ቀኖና፣ ቀኖናዊ ዶግማ፣ እንዲሁም ዶግማ አላት። እነዚህንም የምትቀበልበት ዶክትሪን (አስተምሮ) በዝርዝር አላት። መጽሐፍ ቅዱሳዊና በትውፊት የደረሷትን የእምነት መግለጫዎች ሁሉ ትጠብቃለች፣ ታከብራለችም። መስቀል፣ ታቦት፣ የፆም ስርዓት ወዘተ... መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርጃዎችን አቀናጅታ ትጠቀምበታለች። ለአማኞችም ታስተምራለች፣ እንዲጠቀሙ ታደርጋቸዋለች። የቤተክርስቲያን መሠረታዊ የእምነትና ትምህርት በመጠኑ ሳይረዳ በቀጥታ የመናፍቃንን ትምህርት ብቻ ማንበብ የራሱ የሆነ ተፅዕኖ ይኖረዋል። ስለዚህ ረቀቅ የሚሉ የመናፍቃን ትምህርቶችን የሚመለከት አንባቢ ከቤተክርስቲያን ትምህርት ጋር በማገናዘብ መረዳቱን የበለጠ ማጠንከር ይገባዋል።



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ ሁለት

## የመናፍቃን ማንነት በዘመናት እይታ

በዚህ ክፍል የቤተክርስቲያን ጠላት የሆኑ መናፍቃን እነሳሳቸውን፣ ምን እንዳስተማሩ፣ የኑፋቄው እምነት መስራቾች እነማን እንደሆኑም እንመለከታለን።

### የዘመናቱ አከፋፈል

መናፍቃን በዋናነት የተነሱበትን ዘመን በ5 ከፋፍለን እንመለከተዋለን። እርሱም፡-

1. ከጌታ - 570 ዓ.ም.
2. ከ570 - 1570 ዓ.ም.
3. ከ1570 - 1750 ዓ.ም.
4. ከ1900 - አሁን ናቸው።

### 2.1 ከጌታ ዘመን እስከ 570 ዓ.ም.

ይህ ዘመን በቤተክርስቲያን ታሪክ ምሁራን (Scolar) እምነት እስከ ዛሬ ላለው የመናፍቃን መፈልፈል መሠረት የሆነ የክህደት ትምህርት የተነገበት ጊዜ እንደሆነ ያምናሉ፣ የስተምራሉ። በዚህ ጊዜ ውስጥ በዋናነት ተነስተው የነበሩትንና የኑፋቄያቸው ቅሪት በዚህ ዘመን የሚንፀባረቀውን እንመለከታቸዋለን።



1- **ሀሬ-ጥቃዎች (Judo Xin)**

ሀሬ ጥቃዎች ክርስትናን የተቀበሉ ነገር ግን የክርስትናን እምነት ከሙሴ የኦሪት የመንግት ስርዓት ጋር በመቀላቀል እነዚህን የመንግት ስርዓት የሆኑትን መገረዝ መታጠብ ወዘተን የልተቀበለና የማይፈፅም እንደክርስቲያን እንደማይቆጠር እያስተማሩ የፈሰሰውን የክርስቶስን ደም ከንቱ ያደርጉ ነበር። ይልቁንም በአህዛብ ዘንድ ያለችን ቤተክርስቲያን በማወካቸው የአህዛብ መምህር የሆነው ቅዱስ ጳውሎስ የእነዚህን ሰዎች ትምህርት በስፋት ስህተቱን እየገለጠ ፅፏል። በገላትያ መልዕክት የተጠቀሰው ትምህርትና በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 15 የተጠቀሰው የሐዋርያት ውሳኔ ይህንን ይመለከታል።

ሀሬ-ጥቃዎች፡-

- የክርስቶስን መለኮትነት ከድንግል መወለድ ቢያምኑም ነገር ግን ወደመጨረሻ ይህንን እምነታቸውን ለውጠዋል።
- ከወንጌል በእብራይስጥ ቋንቋ የተፃፈውን የማቴዎስ ወንጌል ይቀበሉ ነበር።

2- **ናዝራውያን (Nazarenes)**

ይህ ስም በመጀመሪያ ለመቀለጃ ለመላው ክርስቲያን ተሰጥቶ ነበር። በኋላ ግን ክርስትና እያየለ ስለሄደ ቅዱስ ጳውሎስን ያስቸግሩ ለነበሩ አይሁድ የተሰጠ ስም ነው።



www.ethiopianorthodox.org

ናዝራውያን ኢየሩሳሌም በ70 ዓ.ም. በጥጦስ እስከተጠፋ ድረስ በፔላ ተገኝ ሆነው ይኖሩ ነበር። ስርዓት ነገራቸው እንደ አይሁዳውያን የመምሰል ባህሪ ነበረው። ይኸውም በዓላትን ማክበር፣ የመንግሥት ሕግጋት መጠበቅ፤ አስመሳዮችን አጥብቀው በመጠበቅና ለዚህም ዋጋ በመክፈል ለጌታ የማያደርግ ስራ ቦታ አይሰጡትም ነበር። ቅዱስ ጳውሎስ በቆላስይስ መልዕክቱ ላይ ምዕራፍ 2፡16 ላይ የጻፈው ናዝራውያንን በመቃወም መልዕክቱን ጽፏል።

## 3- ኢቢዮናውያን (Ebonites)

እነዚህ መናፍቃን አይሁዳዊነትን ያዘለ አመለካከት ያላቸው ነበሩ። ትምህርት ክህደታቸውም፦

- የክርስቶስን ከድንግል መወለድና መለኮትነትን ይክዳሉ፤
- ኢየሱስ ሰው የሆነ የማርያምና የዮሴፍ ልጅ ነው ይሉ ነበር፤
- የቅዱስ ጳውሎስን ሐዋርያነት አይቀበሉም ነበር። ከሕግ የፈነገጠ ከሐዲ ይሉትም ነበር። በአጠቃላይ አይሁዳዊ አስተምሮ በብዛት ይንጸባረቅባቸው ነበር።
- የአይሁድ አማኞች ዛሬም ይህንን ይፈጽማሉ።

## 4- ኤልሴቃውያን (Elkesaites)

ይህን ትምህርት ክህደት የሚያራምዱ ሰዎች የእምነቱን መሠረት ሲገልጡ "ኤልቃ ሲአ" ለተባለው ሰው መልአክ ተገልጦ በሰጠው መጽሐፍ ኢየሱስ ሰማያዊ ከሆኑ ወላጆች የተወለደ መልአክ ነው ብሎ ነግሮታል በማለት ያስተምሩ ነበር።



ከድንግል ማርያም መወለዱን አጥብቀው በመቃወም የመላእክት አለቃ ነው ይላሉ። የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት የሐዋርያው ጳውሎስ ቀዳማዊ የጢሞቴዎስ መልዕክቱና የቆላስይስ ሰዎች መልዕክቱን የጻፈበት ምክንያት የእነዚህን መናፍቃን ትምህርት አጥብቆ ለመቃወም እንደሆነ ያምናሉ።

## 5- ግኖስቲክስ (Gnostics)

ግኖስቲካዊነት በግሪኮች የፍልስፍና አስተሳሰብ የተመሠረተ ክህደት ነው። የክህደት ፍልስፍናው እጅግ የተወሳሰበ በመሆኑ ለአንባቢ እንዲረዳው መሠረታዊ ነገሮችን እንመለከታለን።

ግኖስቲካዊነት ምንድነው?

ግኖስቲክ የሚለው ቃል ወይም ስያሜ የተገኘው ግኖሲስ ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙ እውቀት ማለት ነው። መሠረታዊ የመዳን ሀሳብ (Salivation) በእውቀት ነው ይላሉ።

እምነቱ የሚስማማውን ፍልስፍና ከማያት ቤት፣ ከተለያዩ ፈላስፎች፣ ከአይሁድ ትምህርት ወዘተ በመለቃቀም ምንም እንኳን እንደተደራጀ ሃይማኖት ቢጠራም የብዙ ነገሮች ጥርቅምቅምና ምንጭም (Source) ነው።

### ሀ) ስለፈጣሪ ያላቸው እምነት

እምነቱ የሁለት አምላክ መኖርን (Polythism) ያስተምራል። ሁለቱ አምላክ ክፉና ደግ ብሎ ይጠራቸዋል። ደጉ አምላክ ደግ ደጉን የፈጠረ



www.ethiopianorthodox.org

(ይህም ቁስ አካል ያልሆነውን) ክፉው ደግሞ ክፉ ነገሮችን ሁሉ የፈጠረ ነው ይላሉ።

ከሁለቱ አምላኮች የተለያዩ ትናንሽ አማልክት ተገኙ ከእነዚህም መካከል ዴሚኤርጅ የተባለው ወደታች ወርዶ ምድርን ፈጠረ እርሱም በብሉይ ኪዳን ውስጥ ተጽፎ የሚገኘው ያህዌ እርሱ ነው ብለው ያስተምራሉ።

## ለ. ስለ ክርስቶስ

እምነቱ ስለ ክርስቶስ ሁለት አይነት ትምህርት አለው።

1. ቃል ሥጋ ሆነ የሚለውን በመቃወም ቁስ አካል የሆኑ ነገሮች የተፈጠሩት ከክፉ አምላክ ነው፤ ሥጋ ደግሞ ቁስ ነው ስለዚህ ከደጉ አምላክ የወጣው ሰላሳ ሶስተኛው (33ተኛው) ኤዮንስ ክርስቶስ ሥጋ አለበሰም በሰብአዊ ቅርፅ ተገለጠ እንጂ ይላሉ።
2. ሁለተኛው፤ መለኮታዊ ቃል "ሎጐስ" ሰብአዊ በሆነው ኢየሱስ ላይ አረፈና ወይም አደረና ከስቅለቱ በፊት ተለየው ይላሉ።

## ሐ. ስለድኅነት

ግኖስቲኮች የአዳኛችን ክርስቶስን መገለጥ አያምኑም ይልቁንም ኃጢያትን የሚያያይዙት ከክፋትና ካለማወቅ ጋር ነው። ሰው ለመዳን (እንደነሱ ትምህርት) እውቀት ይኖረው ዘንድ ይገባል ይህም ልዕለ ተፈጥሮዊ እውቀት ነው (Supper natural knowledge) ይላሉ። ክርስቲያን ሳይንስ በዘመናችን ይህንን የመሰለ ትምህርት ያስተምራሉ። ክርስቲያን ሳይንስ በዘመናችን ይህንን የመሰለ ትምህርት ያስተምራሉ።



## 6- መርቅያኒዝም (Mareianism)

ይህ የክህደት ትምህርት የተሰየመው በመስራቹ የሲኖቤው ተወላጅ በሆነው በባለፀጋው መርቅያን ነው። መርቅያን በ139 ዓ.ም. ወደ ክርስትናው መስመር ገብቶ ኑፋቄን የዘራ ሰው ነው። ትምህርቱ ክህደቱም የሚከተለውን ይመስላል።

## ሀ. ስለ እግዚአብሔር

መርቅያን ስለእግዚአብሔር ያለው ትምህርት የግኖስቲክን እምነት የተከተለ ነው። የብሉይ ኪዳንን ሕግ የሰጠው ክፉ አምላክ ሲሆን በክርስቶስ የተገለጠውና ሀዲስ ኪዳንን የሰጠው ደጉ አምላክ ነው ይላል።

## ለ. ስለ ክርስቶስ

መርቅያኒዝም ስለክርስቶስ ሲያስተምር "ክርስቶስ የብሉይ ኪዳን መሲህ አይደለም። በአካለ ሥጋ አልተጋለጠም። የክርስቶስ መገለጥ ግን የብሉይ ኪዳንን አምላክ ለመቃወም ነው። በዚህም ምክንያት አይሁድ ሰቀሉት ብሎ ያስተምራል።

## ሐ. መርቅያን ስለቅዱስ መጽሐፍ ያለው ትምህርት

በቤተክርስቲያን ሊቃውንት እንደሚታመነው ሃዋርያው ቅዱስ አትናቴዎስ የቅዱሳት መጻሕፍን ቁጥር (ቀኖና) እንዲወስን ካነሳሳው ምክንያት የመርቅያኒዝም የክህደት አመለካከት ዘመናትን አቋርጦ እርሱ በነበረበት ዘመን ቤተክርስቲያንን በማወኩ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

መርቃያን የወንጌል መሠረታዊ መልዕክእትና እውነት የገላትያ መልዕክት ነው ይላል። ከወንጌላት ደግሞ የሚቀበለው የሉቃስ ወንጌልን ነው (ለእርሱ እንደሚመችም አዘጋጅቶታል) ከጳውሎስ 10 መልዕክታትን ብቻ ይቀበላል። እነርሱም፦ የመርቃየን ክህደት እስከዛሬ ድረስ በመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና አቀባበል ላይ ተፅዕኖ እንዳሳደረ ይታመናል።

## 7- ሞንታኒዝም (Montanism)

የስነ-መለኮት ሊቃውንት የሞንታነስ አነሳስ በዘመኑ አይሎ የነበረውን ግኖስቲካዊነት በከረረ መልኩ ለመቃወም እንደሆነ ያምናሉ።

ሞንታነስ በተነሳበት ወቅት ጥብቅ የሆነ የሥነ ምግባር መርሆዎችን ይከተል ነበር። እነርሱም ከቅንጦት ምግብ መቆጠብ፣ አብዝቶ መፆም፣ የትዳር ጓደኛ ከሞተ በኋላ ያለማግባት፣ ለሰማዕታትነት መበረታታት ነበሩ። እነዚህ ስርዓቶቹ ታላቁን የቤተክርስቲያን ሰው ጠርጡልያንን ሳይቀር ማርከውት እንደነበር ይነገራል።

### ትምህርተ ክህደቱ

ሞንታነስ ሶስተኛው መገለጥ በእኔ ነው ይል ነበር። አብ በብሉይ ኪዳን በነቢያት ወልድ በሀዲስ ኪዳን በማርያም እንደተገለጠ መንፈስ ቅዱስ ሶስተኛውን መጋለጥ (አስተርዕዮት) በእኔ አደረገ ይላል። እንደውም ትምህርቱን አጠንክሮ ጳራቅሊጦስ ለዓለም ለመናገር የሚጠቀምበት አፈ-መለኮት ነኝ ይል ነበር።



- ይህ መናፍቅ ተከታዮች ከነበሩት መክሲሚላና ጵርስቅላ ከተባሉ ሁለት ሴቶች ጋር በየአደባባዩ በልሳን እንናገራለን፣ ትንቢት ተሰጥቶናል ይል ነበር። ይህንን ድርጊታቸውንና በመንቀጥቀጥ በእብደት መልክ በየጎዳናው የሚፈፅሙትን ሥህተት ታላቁ የቤተክርስቲያን ታሪክ ፀሐፊ አውሳሊዮስ እንዲህ ብሎ ፅፎታል።

"ከፍርግያ ባሻገር ባለው የሚስያ አገር ባለች አንዲት መንደር ውስጥ ሞንታኖስ የሚሉት አስቀድሞ ራሱን ባልተለጐመ የስልጣን ጥም ለጠላት ወቀሳ አሳልፎ የሰጠ ይህ ሰው በቅርቡካመኑት ሰዎች መካከል ያለ ሰው ሲሆን በሆነ እንግዳ መንፈስም ተይዞ የስካር በሚመስል ተመስጦ ውስጥ በመግባት የማይገባ ነገሮችንም እየቀባጠረ ከቀድሞ ጀምሮ ከወረስነው የቤተክርስቲያን ልማድ በወጣ መንገድ ትንቢት ይናገራ" ብሏል። አውሳቢዮስ ይህንን መንፈስ ዲቃላ መንፈስ ይለው ነበር። በዚህ አመለካከት ያሉት ሰዎች ቁርባን እንዳይቀበሉ መከልከላቸውን ፅፏል። Documents of the Christian Church p.77

ሁለተኛው የሞንታኖስ የክህደት ትምህርት በክህነት አገልግሎት ላይ ነው። እንደ ዘመናችን መናፍቃን "ማንም ሰው በተመስጦ ሆኖ መንፈስ ቅዱስ በእማኝ ውስጥ ሲያድር ቤተክርስቲያን በማንም ተራ ግለሰብ ሊመራ ይችላል" ይሉ ነበር። ሞንታነዝም ከዚህ በተጨማሪ የሺ ዓመት አገዛዝ በቅርቡ በክርስቶስ ይሆናል፣ እንዲሁም ከጥምቀት በኋላ የተሰራ ኃጢያት አይሰረይም ይሉ ነበር። የሞንታነስ የክህደት ትምህርት ቤተክርስቲያንን በማወኩ የቤተክርስቲያን መሪዎች ትምህርትንና እንግዳ ልምድን አውግዘዋል። በግዜው የነበሩ የአረማውያን ሃይማኖቶች ምንታኒዝሞች እንደሚያደርጉት አይነት በጣዖቶቻቸው ፊት ይንቀጠቀጡ



www.ethiopianorthodox.org

ስለነበር የሞንታነስ ተግባር ለቤተክርስቲያን ማፈሪያ ሆኖ ነበር። በጉባኤ ቈስጥንጥንያ የኒቂያ ጉባኤን የሃይማኖት መግለጫ የተመለከተው ጉባኤ ካወገዛቸው የሃሡት ትምህርቶች አንዱ የሞንታነስ ክህደት ነው። ጊዜውም በ381 ነው።

## 2.2 አዕራረ ሥላሴ

በዚህ ርዕሱ ዙሪያ የምንመለከታቸው መናፍቃን የሥላሴን ትምህርት በመቃወም የካዱትን መናፍቃን ነው። ትምህርታቸው አሀዳዊነት ወይም አንድ ገፅ (Monorchianism) ይባላል።

### 1- ሁለቱ የአሀዳዊነት (ሞኖርኪያኒዝም) አስተምሮ

የፀረ ሥላሴ አቋም ያላቸው መናፍቃን በአሀዳዊነት ወይም አንድ ገፅ ትምህርታቸው በሁለት ጐራና አመለካከት ይከፈላሉ። እነርሱም፡-

#### ሀ. ጳውሎስ ሳምሳጢያዊ አመለካከት

በጳውሎስ ሳምሳጢና በቢዛንታይኑ ቴዎዶቶስ የተሰጠው የአሀዳዊነት (አንድ ገፅ) ትምህርት አደገኛ፣ ሀይለኛ (Dynamic) የሚባለው ነው። የክህደቱ መስራች ጳውሎስ ሳምሳጢ የስላሴን እምነት በመካድ ስለአንድ ገፅ የሚከተለውን ያስተምራል

"ቃል (ሎጐስ) የሰው ሀሣብ (reason) በሰው ልብ ውስጥ ልብ ውስጥ እንዳለ ሁሉ ቃልም በእግዚአብሔር ውስጥ ይኖራል እንጂ ጉልህ አካል አይደለም፡ ማለትም እርሱ አካላዊነት የሌለው ኃይል ነው። ነገር



ግን በማርያም ልጅ በኢየሱስ ውስጥ በዮርዳኖስ ሲጠመቅ በአብ ሕልውና ውስጥ የኖረው ቃል አደረበት በማደጉም የእግዚአብሔር ልጅ ተባለ" በማለት የክህደት ቃሉን ያስተምራል። ይህ ክህደት ሀድረት (Adoptianism) ይባላል።

#### ለ. ሰባልዮሳዊ አመለካከት

የሊቢያ ተወላጅ በሆነው በሰባልዩስ የተሰጠው የአንድ ገፅ ትምህርት "ቅርፃዊ" "modalistic" ይባላል።

ቅርፃዊነትን ሰባልዩስ ሲያስተምረው፡- "እግዚአብሔር አንድ አምላክ ሆኖ በተለያየ ጊዜ በተለያየ ቅርፅ እራሱን ገለጠ ማለትም በብሉይ አብ፣ በሀዲስ ወልድ፣ በዘመነ ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ መልክ ተገለጠ" ብሎ ያምናል። በቀላል አገላለፅ አብ እንደ ወልድ ተወለደ፣ ተሰቀለ፣ እንደ መንፈስ ቅዱስ ወረደ እንደማለት ነው። በዘመናችን የዚህ ክህደት ቀጥተኛ አስተማሪዎች የሐርያት ቤተክርስቲያን የተባለው Only Jesus ነው።

### 2- አርዮሳዊነት (Arianism)

በቤተክርስቲያን ትምህርት በፀረ-ስላሴ ትምህርቱ የታወቀው መናፍቅ አርዮስ ነው። የአንድ ገፅ ትምህርት አስተማሪዎችን እነ ሰባልዩስን የተቃወመ መስሎት "ለወልድ መኖር ጅማሬ አለው የእርሱም ሕልውና ያልነበረበት ጊዜ ነበር። ወልድ ፍጡር በመሆኑ፣ አብ እርሱን ፈጥሮ ዓለምን ፈጠረበት በማለት ክዷል።"



www.ethiopianorthodox.org

አርዮስ ስለመንፈስ ቅዱስ ሲያስተምር "የመጀመሪያ የወልድ ፍጡር ነው ብሏል። በዘመናችን አርዮሳዊነትን በቀጥታ የሚያስተምሩት ጀሆቫዊትነስ ወይስ የዩህዋ ምስክር ናቸው።" አርዮሳዊነት በ325 በኒቂያ የተወገዘ ክህደት ነው።

## 3- መቅዶንዮሳዊነት

የአርዮሳውያን ኑፋቄ በመጋራት "መንፈስ ቅዱስን ታናሽ (ሀሀዕ) ወይም መለኮትነት የጐደለው እንደመላዕክትም ያለ ፍጡር የወልድም ተገዥ በማለት ክዷል።" መቅዶንዮሳዊነት በ381 በጉባኤ ቁስጥንጥንያ የተወገዘ ክህደት ነው።

## 4- ንስጥሮሳዊነት

ንስጥሮሳውያን ፀረ-ማርያም ነው። የእመቤታችን ወላዲተ አምላክነት ክዶ "ማርያም ወላዲተ አምላክ ሳትሆን ወላዲተ ክርስቶስ ናት" በማለት አስተምሯል። የሁለት ባህርይና ሁለት አካልን ያስተማረ መናፍቅም ነው። ንስጥሮሳዊነት በ435 በኤፌሶን የተወገዘ ክህደት ነው።

እነዚህን ፀረ ሥላሴ እምነት የነበራቸውን ሰዎች የቤተ ክርስቲያን አምድ የሆኑ ሊቃውንት በተለያየ ግዜ በመነሳት ትምህርተ ክህደታቸውን ነቅለው ጥለዋል። በጽሁፍ ምላሽን በቃልም ትምህርትና ተግሳፅን ሰተዋል። ከእነዚህም የሚጠቀሱት አባቶች ሐዋርያዊ አትናቴዎስ ቄርሎስ ባስልዮስ ዮሐንስ አፈወርቅና ሁለቱ ጐርጐርዮስ ተጠቃሾች ናቸው።



## ማጠቃለያ

በዚህ በተመለከትነው ዘመን የመናፍቅነቱ አካሔድ አንዱ አንዱን የሚጐትትበት እይታ ነበር። ስላሴን አስመልክቶ የተነሳው ክህደት በክርስቶስ የባህርይ አምላክነት ላይ፤ በክርስቶስ የባህርይ አምላክነት ላይ የተነሳው ክደት በሥላሴ እምነት ላይ ክህደትን ያመጣ ነበር።

እንዲሁም የክርስቶስን እውነተኛ መለኮትነት የሚክዱ ባንድ ወገን፣ እውነተኛ ስብዕናው (የሥጋ መልበሱን) ደግሞ በሌላ ወገን የሚክዱ መናፍቃን በየጊዜው ሲነሱ አንዱ አንዱን እቃወማለሁ፤ በማለት ከአማናዊት ቤተክርስቲያን ትምህርት እያፈነገጠ የኑፋቄው ዘርፍ ይበዛ ነበር።

ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ዶሴታውያን የኢየሱስን ስብእና፣ ኢቦናውያን ደግሞ መለኮትነቱን፣ አርዮሳውያን መለኮትነቱን ገዞ ሲያደርጉ አቡሊናርዮሳውያን ደግሞ ሰውነቱን አሳንሰው ንስጥሮሳውያን የሁለት ባህርይን ውህደት (ተዋህዶ) ሲክዱ አውጣኪያን ደግሞ የክርስቶስን አንድ ባህርይ ብቻ ያፀኑ ነበር። በዚህም መጠላለፍ ምክንያት እውነተኛው የወንጌል ዘር ላይ ሰይጣን እንክርዳዱን ይዘራ ነበር። ክህደቱን ይዘው የሚነሱት ሰዎችን የቤተክርስቲያን ጠበቆችም ያስመስላቸውም ነበር። በዘመነ ሰማዕትነት ከነበረው በበለጠ የመናፍቃን ሰይፍ ቤተክርስቲያን ተዋግቷት ነበር መባሉም ለዚህ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ በዚህ መልክ በመናፍቃን ጥቃት እስከ 451 የዘለቀች ቤተክርስቲያን ይህንን ሁሉ ጥቃት በመቋቋም በእምነት ብትፀናም ፖሎቲከኞች (Polotics) ቤተክርስቲያንን መጠቀሚያ በማድረግ ከ570-1575 ስፊውን ዘመን የተሳሳተ አስተምሮ ለዘራችው የሮማ ቤተክርስቲያን ምቹ ወቅትን ፈጠረለት።

ከዚህ በመቀጠል የምንመለከተውም ምዕራፍ በሮማ ቤተክርስቲያን በዚህ ጊዜ የተፈፀሙና የተነሱ የስህተት ትምህርቶችን ነው።



# ምዕራፍ ሶስት

## መናፍቅነት ከ570-1517

በዚህ ርዕስ ውስጥ በሮማ ቤተክርስቲያን ተነስተው የነበሩትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑና ከቤተክርስቲያን ጉባኤያትና ቀኖና የወጣን የስህተት ትምህርቶችን በዝርዝር እንመለከታቸዋለን።

### 3.1 ፊሊክዌ (Filiogue) ሁለትዮሽ ስርዕት

የሃሳቡ አመንጭ ፓፓ ቤኔዲክት ነው። ፊሊክዌ ማለት "ዘሠረፀ እምአብ ወወልድ" ነው። መንፈስ ቅዱስ ከአብም ከወልድም የሰረፀ ማለት ነው።

ቤተክርስቲያን በጉባኤ ቁስጥንጥንያ ያፀናችውን እምነት በመለወጥ በ589 ዓ.ም. በቶሌዶ (Toledo) እንዲሁም ወልድ የሚለውን ሀረግ የሮማ ካቶሊካዊት በኒቂያ የሃይማኖት መግለጫ (Creed) ላይ ጨመረች። በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ 16 ቁጥር መጨረሻ የተጠቀሰውን ትክክለኛ ትምህርት በመቀየር የሮማ ቤተክርስቲያን ድርብ ስርፀትን (Double procession) ስታፀና ኦርቶዶክሳዊያን ግን ነጠላ ስርፀትን (Single procession) ይዘው 1054 ዓ.ም. ተለያይተዋል።

### 3.2 አስቀድሞ የመወሰን ትምህርት (Pre-destination)

የሮማ ቤተክርስቲያን የዚህን ትምህርት እምነቷን ስትገልጥ "እግዚአብሔር በዘላለማዊ ድንጋጌው ሁሉንም ነገር አስቀድሞ ወስኗል።



www.ethiopianorthodox.org

ሰዎች ለእግዚአብሔር ጥሪ የሚሰጡትን መንፈሳዊ መልስና በተቃራኒውም ስለሚያውቀው እጣቸውን ወስኗል። በዚህም መሠረት አንዳንዶችን ለድኅነት ሌሎችን ደግሞ ለዘላለም ኩነኔ ተመድበዋል ትላለች።" ይህም ከኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን የተለየ ትምህርት ነው።

## 3.3 <u>መካነ ንስሐ (Pergatory)</u>

የሮማ ቤተክርስቲያን የንፍሳት ጊዜያዊ ስፍራ ወይም ማቆያ እንዳለ ታስተምራለች። ስፍራውንም መካነ ንስሐ (ፐርጋቶሪይ) ትለዋለች። የመካነ ንስሐን ትምህርት ከመመልከታችን በፊት ወደዚህ ገብዛው የሚያደርሰንን የሮማ ቤተክርስቲያንን የንስሐ ስርዓት እንመልከት።

በሮማ ቤተክርስቲያን ትምህርት መሠረት ሁለት አይነት ኃጢያቶች አሉ። ቀላል እና ከባድ ይባላሉ።

ቀላል ኃጢያት አነስተኛ የሆኑና የኃጢያተኛውን ድኅነት የማያሳጡ ናቸው። "በቀላል" ኃጢያት የተያዘውን ሰው እግዚአብሔር በዚህ ምድር ላይ በማስቃየት ወይም በሞት ግዜ በመካነ ንስሐ (ፐርጋቶሪይ) ፍርድ ይቀጣዋል። ከባድ የሚባለው ኃጢያትን ግን የኃጢያተኛውን ድኅነት የሚያሳጡ ሲሆኑ ቀኖናቸው ለዚህ አይነት ኃጢያት ስርዓትን ደንግጓል።

የንስሐ አፈፃፀሙም በሮማ ቤተክርስቲያን ሶስት አይነት ነው።

1. ሀጢያተኛው እራሱ መናዘዝ
2. ለካህን መናዘዝ



3. ስለኃጢያቱ የሚያስደስት ክፍያን መፈፀም።

እንግዲህ የመካነ ንስሐ (Pergatory) ትምህርትና የስርየት ካርዱ (ኢንዶልጀንስ) ሽያጭ የመጣው በሶስተኛው የንስሐ ስርዓት ተመርኩዞ ነው። ሟች ከመካነ ንስሐ በቶሎ እንዲወጣ ቤተሰቡ በቂና ጠቀም ያለ ገንዘብን መክፈል እንደሚያስፈልግ ይሰብክ ጀመረ። ይህ ሃይማኖታዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊነት የሌለው ትምህርት ነበር። ምክንያቱ (cause) የሮሙን ጴጥሮስ ካቴድራል ለመጨረስ በሥጋ የተወጠነ ነገር ግን መንፈሳዊ ስህተት የነበረበት የእግዚአብሔር ቸርነትና ጸጋን የሚያቃልል ነበር። ይህም ለብዙዎች መሰናክል ሆኖ ብዙ መናፍቃን እንዲነሱ አድርጓል።

## 3.4 <u>የፓፓው ፍፁምነትና ስግደትም እንደሚገባው ማመን</u>

•

የሮማ ፓፓ የማይሳሳት ፍፁምነት (Absolutism) የተጀመረው በጐርጐርዮስ ሰባተኛ ነው። በስሙ በሚታወቅ "Dictate of Hilderbrand " በተሰኘው 26 ነጥብ በያዘው ጽሁፍ የሚከተሉት ከእግዚአብሔር ቃልና ከክርስቶስ ትምህርት ጋር የሚቃረኑ ትምህርቶች ተቀምጠዋል። አራቱ ነጥቦች በሚከተሉት ቁጥሮች ተራ ላይ ተቀምጠዋል።

- ☞ ነጥብ 2 የሮም ጳጳስ በራሱ ፍጹምና አለም አቀፋዊ ነው።
- ☞ ነጥብ 9 ልዑላን (የምድር ነገስታት) እግሩን ብቻ መሳም (መስገድ) አለባቸው።
- ☞ ነጥብ 19 ጳጳሱ በማንም ሊከሰስና ሊፈረድበት አይችልም።
- ☞ ነጥብ 22 የሮም ቤተክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ጥንትም አሁንም ሆነ ወደፊት ልትሳሳት አትችልም።



www.ethiopianorthodox.org

እነዚህን ነጥቦች በቃለ እግዚአብሔር ስንመዝን ፍፁም የፈጠራ ስራዎች እንጂ ከቃሉ ጋር ተዛምዶ ያላቸው አይደሉም። ዛሬ አንሳሳትም በሚሉት ሮማውያን እየተፈፀሙ ያሉት አስደንጋጭ ስህተቶች በቅርብ በዓ ለም አቀፍ ታላላቅ መገናኛዎች ሲደመጡ ነበር።

እንዲሁም የሚከተሉት የተጋነኑና ምድራዊ "አምላክነት" የሚያሰኝ የክብር አጠራርም ይሰጠዋል።

1. "በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ክርስቶስ በቤተክርስቲያን ላይ ስልጣን እንዳለው የሚናገሩት ጥቅሶችና ለእርሱ የተሰጡ ስሞች በሙሉ ለጳጳሱ ሊውሉ ይችላሉ" Berlamin, on the Authority of Council's Book 2, Chapter 17 ላይ ይገኛል።
2. "እነሆ አንተ (ጳጳስ) እረኛ፣ ሐኪም፣ መሪ፣ የቤተክርስቲያን ሙሽራ ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ በዚህ ምድር ላይ አምላክ ነህ።" Labbe and cossarts "History of the Councils vol. XIV Col. 109 ላይ ይገኛል።
3. "አንተ ጳጳስ አባ፣ ጌታ፣ እግዚአብሔር ነህ" Extrauagante, of the Pope John XXII title 14: Chapter 4 ላይ ይገኛል።

ከዚህ ጋር በ1302 ዓ.ም. ቦኒፌስ ስምንተኛ (Boniface VIII) የተባለው ፓፓ የሮም ጳጳስ በሁለት ዓለማት ላይ ስልጣን አለው። በመንፈሳዊም በዓለማዊም ሰይፍ ይቀጣል ሲል አውጇል። ይህንን የጳጳሱን አባባል የቤተክርስቲያን ሊቃውንት "የተጠረበና የለዘበ እንጨትና ድንጋይ ታመልክ የነበረችው ሮማ ቀስ በቀስ ሥጋና ደም ያለው ጣዖት ማምለክ ጀመረች" ብለዋታል።

ቤተ ክርስቲያኗ ከዚህ ሁሉ ጋር፦



- ሃይማኖታዊ አኗኗር ላይ ከማተኮር በሰዎች ሥጋዊ አኗኗርና ክብር አተኩራ ነበር።
- የእግዚአብሔርን ሥራ በማወጅና ክብርን ከመስጠት ይልቅ የሰዎችን ሥራ በማውራትና ለሰዎች ክብርን በመስጠት ታተኩር ነበር።
- በእግዚአብሔርና በመንግሥቱ (በመንግሥተ ሰማያት) ላይ ባሉ ነገሮች ላይ ያለውን ፍላጐት ከማጠንከር ይልቅ መሪዎቿ በዓለምና በምድር ባሉ ነገሮች ላይ ፍላጐት ጠንክሮ ይታይ ነበር። በዚህ ምክንያት መጽሐፍ ቅዱሳዊና የአባቶች ትምህርት ላልሆነ የስህተት ትምህርት መንገዱን ከፍታ ነበር።

## 3.5 <u>የቁርባን ስርዓት በቤተክርስቲያና</u>

ሮማ ቤተክርስቲያን ከምታከናውነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ካልሆኑ ስርዓቶች አንዱ የቁርባን ስርዓቷ ነው። በሮም ቤተክርስቲያን በማቴ. 26፥27 "ከእርሱ ሁላችሁ ጠጡ" የሚለውን የጌታን ቃልና የጥንታዊ ቀኖና ስርዓትን በተቃወመ መልኩ ሥጋ ብቻ ታቀብላለች።

የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ከጽዋው ምዕመናን እንዳይጠጡ የከለከለችው 1401-1404 ባለው ጊዜ ነው። የጥንት ቤትክርስቲያን ስርዓት ግን ሁለቱንም ማቀበል እንደነበር ጀሮም እንዲህ ሲል ጽፎታል "የቅዱስ ቁርባንን ምስጢር የሚያከናውኑት ቀሳውስት የክርስቶስን ደም አካፍለው ለህዝቡ ይሰጣሉ" ብሏል። ይሁንና የሮም ቤተክርስቲያን ለዘላለም አልሳሳትም ማለቷ ስህተት መሆኑን ይህ ያመለክታል።



www.ethiopianorthodox.org

## 3.6 ኢኮኖላትሪያ (Iconoclasitc)

አይከን ሃይማኖታዊ ምስል ማለት ሲሆን ኢኮኖላትሪያ ማለት ግን ምስልን መስበር ማለት ነው በግሪክ ቋንቋ። የዚህ ትምህርት ክርክር በከፍተኛ ሁኔታ የተባባሰው በ726 ዓ.ም. ነው። በዚህ ወቅት የነበረው ንጉስ ሊዮ ማናቸውንም ለምስል የሚደረግ አምልኮን ቢከለክልም ጎርጎርዮስ አንደኛና ሁለተኛ ግን ተቃውመውታል። ይሁንና 787 ዓ.ም. የሮም ካቶሊክ የተቀረፀ ነገርን ለማክበር ስትወስን የምስራቅ ቤተክርስቲያን ግን 843 ዓ.ም. ቅርጽን ማለት ከድንጋይ ከብረትና ከእንጨት የተቀረፁትን በማስወገድ በስዕል ወይም በምስሎች ብቻ እንዲሆን ወሰነች።

ታላቁ የቤተክርስቲያን አባት ባስልዮስ (Basil the great) "ለተቀረፁ ምስሎች የሚሰጥ ማንኛውም አክብሮት ውሎ ሲያድር ወደ አምላክ ምሳሌነት ሊለወጥ ይችላል በማለት የተቀረፀ ምስልን መጠቀም ወደሌላ አምልኮ እንደሚጋብዝ አስጠንቅቋል። ቅዱሳት ስዕላት በመጽሐፍ ቅዱስ የመገናኛው ድንኳን (ደብተራ ኦሪት) ስትሰራ የመላዕክቱን የኪሩቤልን ስዕል እንዲሰራ ሙሴ በእግዚአብሔር የታዘዘ ሲሆን ሰሎሞንም ቤተመቅደሱን ሲሰራ ሕገእግዚአብሔርን ጠብቆ ስዕሉን ማሳሉ በቅዱስ መጽሐፍ ተገልጧል።"

በሀዲስ ኪዳንም የጥንት ክርስቲያኖች የቀደሙ የእምነት ሰዎች አገልግሎትና የክርስትናን ታሪክ ሒደት ትውስታን የሚቀሰቅሱ ሲሆ ከስዕሉ ባለቤት ጋርም እንዲገናኝ ያደርጋል። ይልቁንም ጽሁፍ መጠቀ ባልተቻለበት ወቅት በካታ ኮምብ (ግበበ ምድር) የጥንት ክርስቲያኖ



የቀደመውን የእምነት ታሪክ ለልጆቻቸው በስዕሉ ያስተምሩ እንደነበር የቤተክርስቲያን ታሪክ ያስተምረናል።

### ማጠቃለያ

በዚህ የኑፋቄ ዘመን ከእነዚህ ውጭ በተለያዩ ሃይማኖታዊና የስርዓት ህጐች ላይ የተዘሩ ኑፋቄዎች ሲኖሩ ከነዚህም የሁለት ባህርይ ትምህርት፣ ጉዳይ የካህናት (ቀሳውስት) ያለማግባት ውሳኔ ወዘተ ይገኙበታል።

ምንም እንኳን አንዳንድ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት በዓለም አቀፍ ትብብር (Ecummunism) መንፈስ የሮም ቤተክርስቲያን ከብዙ ኦርቶዶክሳዊያን ቤተክርስቲያን ስምምነት እያደረኩኝ ነኝ እንዲሁም የተለያዩ አስተምሮዎቶቿ ላይ መግባባት ፈጥረናል ብትልም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የዚህ እንቅስቃሴ መኖሩን እንደማይታወቅ ሊቃውንትን ጠይቄ ተረድቻለሁ።



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ አራት

## መናፍቅነት ከ1517-1750

ከ570-1517 በሮም ቤተክርስቲያን ላይ ከተከሰቱት የጉላ ስህተቶች አንዱ የሆነው ከመካነ ንስሃ ነፍሳትን ለማውጣት በሚለው የስርየት ካርድ ሽያጭ (ኢንደለጀንስ) ምክንያት ሉተር አፈንግጦ በመውጣት ዘጠና አምስት አንቀጽ የያዘውን የእምነቱን አቋም በማወጅ ተቃውሞ የጀመረበት ጊዜያት ለዚህ ችግር መከሰት መጀመር የመጀመሪያው እምርታ ነው።

## 4.1 ማርቲን ሉተርና ትምህርተ ክህደቱ

### ሉተር ማን ነው (Who is Lutter)

ሉተር በ1843 አይስሌበን ሳክሶኒ (Eislebe Saxony) ከገበሬ ቤተሰብ የተወለደ ሰው ነው። የተለያዩ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ሉተር በሕይወቱ ፈታኝ ግዜ ከነበረው የመብረቅ አደጋ ከተረፈ በኋላ ለቅድስት ሀና ስዕለት ተስሎ ነበር። ስዕለቱ ቀሪ ሕይወቱን በምንኩስና ለማሳለፍ ሲሆን በገዳም በመሆኑ በገዳም ኑሮውን ጀመረ። ይሁንና ብዙ ግዜ ሳይቆይ የገዳም ኑሮውን በመተው ለቆ ወጣ። ሉተር ገዳሙን ለመልቀቁ የተለያዩ ምክንያቶች ይቀርባል።

ከገዳሙ ሕግ ውጭ መነኩሴ የሆነችውን ማርጋሬታን በማግባቱ፤
የሮማ ቤተክርስቲያን ጳጳሳትን አሰራር በመቃወሙ፤
በሮሜ1፥17 ያለውን ቃል ትርጉም በተሳሳተ መልኩ በመረዳቱ፤



4. እምነት እንጂ ምግባር አያስፈልግም፤ የገዳም ኑሮ በሥራ ለመጽደቅ መጣር ነው ብሎ በማለቱ፣ እንደወጣ ይታመናል።

### 4.1.1 የሉተር ትምህርተ ክህደት

ሉተር የሚከተሉትን የስህተት ትምህርቶች አስተምሯል።

#### ሀ) እምነት ብቻ (Sola fide /only faith)

ሉተር የሰው ልጅ ለመዳን እምነት እንጂ ምግባር (ሥራ) አያስፈልገውም ይላል። ቅዱስ ያዕቆብ በመልዕክቱ እምነት ያለምግባር ምግባር ያለእምነት የሞተ እንደሆነ ጠቅሶ የጻፈውን ሳይቀር በመንቀፍ <u>"ያዕቆብ በመንፈስ ሳይሆን (inspired) የጻፈው ነው"</u> እስከማለት ደርሷል። አንዳንድ ሊቃውንት ሉተር በዚህ ሃሳብ ሊፀና የቻለው በገዳሙ በዝሙት (በምግባር አልባነት) በመከሰሱ መሆኑን አጥብቀው ያስተምራሉ። በተለይም በገዳም ውስጥ ያለውን የጸሎትና የፆም ኑሮ ስርዓትና ሥጋን ለመግዛት የሚደረገውን ሉተር ይቃወም ነበር። ከዚያም ጋር በሥራ ሊገለጡ የሚገባቸውን ነገር በመተው በጸጋው ድነናል የሚለውን ይሰብክ ነበር።

#### ለ) ምስጢረ ክህነትን ይቃወማል።

ሉተር ምስጢረ ክህነትን አይቀበልም፤ ሁላችሁም ካህናት ናችሁ ለካህን ኃጢያትን መናዘዝ አያስፈልግም በማለት ይክድ ነበር። ይህ ሉተር በሮም ጳጳሳት የሚደርስበትን ውግዘት ለማምለጥ የተጠቀመበት ብልጠት ነበር። የክህነትን አስፈላጊነትና ኃጢያትን 'ለካህን ስለመናዘዝ የጥንት ቤተክርስቲያንና ጌታም በቅዱስ ቃሉ ያዘዘው መሆኑን እያወቀ ይህን



www.ethiopianorthodox.org

ማድረግ ክህነቱን አፍርሷል የሚለውንም ለመሸፈን ጭምር ያነሳው ክህደት ነው።

ካህናት የማሰር የመፍታት ስልጣን እንዳለቸው የሚያምነውን ሕዝብ ከዚህ መስመር እንዲወጣ ሉተር በማድረግ ሁሉ በራሱ መንገድ እንደጓገ አድርጉታል።

**ሐ) <u>ቅዱስ መጽሐፍ ብቻ (Sola Scripture)</u>**

ሉተር ይህንን ትምህርት የሚያስተምረው "የአማኞች ብቸኛ ባለሥልጣን መጽሐፍ ቅዱስ እንጂ ቤተክርስቲያን አይደለችም።" በማለት ነው። የሃይማኖት ውሳኔዎችን ሁሉ አይቀበልም ነበር በትውፊት የደረሱ የቤተክርስቲያን ስርዓቶችንም ሁሉ ያጣጥል ነበር።

ዛሬ እንደ አሸን ለፈላው የስህተት ትምህርት ምክንያቱ መጽሐፍ ቅዱስን ሁሉ እንዳሻው መተርጉም ይችላል በማለት የቤተክርስቲያን ስልጣን ለግለሰብ ሉተር በመስጠቱ ነው። ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን መጽሐፈ ቅዱስን ተርጉማ ለምዕመናን የምትሰጥ ቤተክርስቲያን ብቻ መሆኗን ታምናለች። የአማኞችም ባለሥልጣን ቤተክርስቲያን ናት። የቤተክርስቲያን መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ "...ቢበድልህ ለቤተክርስቲያን ንገራት..." እያለ የቤተክርስቲያን ስልጣን በአማኞች ላይ መሆኑን አስተምሮናል። እንዲሁም በጽሁፍ ያልተፃፉ ነገር ግን በትውፊት የደረሱትን የእምነት ስርዓቶችን ቀኖናዎችን ወዘተ ቤተክርስቲያን ትቀበላለች። ቤተክርስቲያን ቅዱስ መጽሐፍን እራሱን በትውፊት መቀበሏን ታስተምራለች። በቤተክርስቲያን ትምህርት ከጽሁፍ በፊት ትውፊት ይቀድማልና ነው።



**መ) <u>ለሞቱ ሰዎች መፀለይ፣ እንዲሁም በቅዱሳን ስም መፀለይን ይቃወማል።</u>**

ይህ አራተኛው የሉተር የስህተት ትምህርት ነበር። የስርየት ካርዱን (ኢንዱሊጀንስ) ሽያጭ የተቃወመ መስሎት በመጽሐፍ ቅዱስና በቤተክርስቲያን ቀኖና በግልጽ ያለውን፦

- ለሞቱ ሰዎች መፀለይ
- በቅዱሳን ስም ምልጃን መጠየቅን በመካድ ኑፋቄን ዘራ።

ይሁንና የጥንት ቤተክርስቲያን በስርዓቷ ለሞቱ ሰዎች ትፀልይ ነበር። በመጠራታቸው ወቅት ፍፁምነት በሁሉም አይገኝምና እግዚአብሔር የሞቱትችውን ነፍስ እንዲምር ትጸልያለች። ቅዱስ ጳውሎስ በመልዕክቱ ለሞተው አገልጋዩ ለሄኔሲፎሩም "ጌታ ነፍሱን ይቀበል ለቤተሰቡም መፅናናት ይስጥ" እንዳለ በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ተጽፎ እናገኛለን። በዚህም መልክ ሟች በጌታ ፊት ክብር እንዲያገኝና አማኞች በምድርና በሰማይ ያለችውን አንድነት ለመግለፅ፣ የነፍስን ህያውነት ለማዘከር ለሞቱ ሰዎች ይፀለያል። ቤተክርስቲያን ይህንን ስርዓትም ታከናውናለች።

የሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስለቅዱሳን ምልጃና ስለሞቱ ሰዎች መፀለይ ይገልጣል።

ዘጸ.32፥9-12 የሐዋ.19፥11 ዘዳ. 9፥18 ዮሐ. 14፥12 መዝ. 106፥23
ራዕ.6፥92ነገ.4፥33 1ነገ.13፥13 2ነገ.13፥2 ማቴ. 9፥8 ወዘተ



www.ethiopianorthodox.org

## ማጠቃለያ

የሉተርን ትምህርት እምነት (ካቴኪዝም) አብዛኛው የፕሮቴስታንት ዲኖሚኔሽን የተቀበለው ሲሆን በተለይም የሉተር ስነ መለኮት ተከታዮች በ1530 የወጣውን የአወግስበር (Aussburg) ውሳኔ ይቀበላሉ። እርሱም፡-

- አንድን ሰው ፃድቅ ብሎ መሰየም አግባብ አይደለም።
- ሰው ደኅንነትና ጽድቅ ለማግኘት የሚያስፈልገው በእምነት ብቻ ነው።
- ኃጢያትን ለካህን መናዘዝና ክህነት አያስፈልጉም።
- የጌታ እራት (ቁርባን) በሚወሰድበት ግዜ ክርስቶስ በሕብስቱና በወይኑ ከላይና ከታች ይሆናል (consubstantion) እንጂ አይለወጥም ይላሉ። ከዚህም ጋር የሁለት ባህርይ ትምህርትና የሁለትዮሽ ሥርጻትን እንደሮማ ቤተክርስቲያን ይቀበላሉ።
- ታሪክ እንደሚያስገነዝበን ሉተር በጀርመን እምነቱን ለማስፋፋ የተጠቀመበት መንገድ ፍጹም ቅዱስ መጽሐፍን የተከተለ አልነበረም። በወቅቱ የነበሩትን ገዥዎች ተጠግቶ እጅግ ብዙ የጀርመን ገበሬዎችን አስፈጅቷል።
- በመስቀል ሞት ክርስቶስ ዓለምን የወደደባትን ፍቅሩን ጦር አስብቆ ከፖለቲከኞች ወግኖ ኑፋቄን መዝራት የአመፀኞች ግብር መሆኑን ልብ ይለዋል።

## 4.2 ጆን ካልቪንና ትምህርተ ክህደቱ

ከ1517-1750 ያለውን የመናፍቃንን እንቅስቃሴ በምናጠናበት ወቅት ከሉተር በመቀጠል እምነመለከተው ካልቪን ነው።



## ካልቪን ማን ነው? /Who is John Calvine/

ይህ ሰው 1509 በፈረንሳይ የተወለደ ሰው ነው። በ1534 የተዛመተውን የፕሮቴስታንት ትምህርት ተቀብሎ በሀገሩ ቢያስፋፋም በመንግሥት ተባሮ ቀሪ ጊዜውን በስዊዘርላንድ ያሳለፈ ሰው ነው።

ካልቪን ፖለቲከኝነት በጉልህ የሚታይበት ሰው ስለነበር በስዊዘርላንድ ከመሪዎች ጋር በመተባበር ብዙ ሰዎች አመለካከቱን አልቀበልም ሲሉ በሞት ይቀጣ ነበር። በወንጌል ሽፋን ለገዥዎች ያደረው ይህ ሰው በታሪክ የማይረሳውን ሴርቬተርስ (Servetus) የተባለን ሰው በእሳት ተቃጥሎ እንዲሞት አስበይኖበታል።

በጌታም ሆነ በሐዋርያት ያልተፈፀመና የፍቅር አገልግሎ የሆነውን የክርስትና ትምህርት በዚህ መልክ ማከናወን አመፅ ነው። የሚያጠፋና በስህተት የተያዘ ሰውን አባቶቻችን እንዲያምን ያስተምራሉ፤ እምቢ ቢል ያወግዛሉ እንጂ ሕንፃ ስላሴን ለማፍረስ አንዳች እርምጃን አያደርጉም። ካልቪን ግን ከዚህ የተለየ ነበር።

## የካልቪን የክህደት ትምህርት

ካልቪን የሉተርን ካቴኪዝም በመቀበል የሚያራምድ ሲሆን የሚከተሉት ደግሞ የራሱ የስህተት ትምህርቶች ናቸው።

- የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሳይንሳዊ መሆን አለበት ይላል፤ (ቅ/ጴጥሮስ የመጸሐፍ ቅዱስን ቃል በመንፈስ ቅዱስ መተርጉም የሚለውን አይቀበልም)።



www.ethiopianorthodox.org

- አስቀድሞ መምረጥ (መወሰን) አጥብቆ ያስተምራል፤ እግዚአብሔር ሰዎችን ለፅድቅና ለኃጢያት ወስኗል (Perdistination) ይላል።
- ድኅነት ከቤተክርስቲያን ውጭ ይገኛል ይላል። ይህ ማለት በሚስጥራት ቤተክርስቲያንና በምስጢረ ክህነት አያምንም።
- የጌታ እራት (ቅዱስ ቁርባን) መታሰቢያ (Remebrance) ነው ይላል።

ካልቪን በእነዚህና በሌሎች ስህተቶች ታጅቦ ቤተክርስቲያንን ለዘመናት ያወካት መሆኑን በታሪክ እንረዳለን።

በዚህ ዘመን እጅግ ብዙ የሚሆኑ መናፍቃን እንደነ ዚዌንግሊንና የአናባብቲስት ያሉ በድርጅት የተመሠረቱና የሕፃናትን ጥምቀት የሚቃወሙ፣ የክርስቶስን ሥጋና ደም መታሰቢያ የሚሉ የተነሱበት ዘመን ነበር።

ይሁንና በብዙዎቹ አስተምሮአቸው በመመሳሰሉ የክህደቱ ፊትአውራሪ የሆኑትን ሁለቱን ብቻ መመልከቱ በቂ ነው።

በመቀጠልም ጠለቅ እያለና ከአማናዊት ቤተክርስቲያን ትምህርት ያፈነገጡ የክህደት ትምህርቶችን እንቃኛለን።



# ምዕራፍ አምስት

## መናፍቅነት ከ1750-19..

በምዕራፍ አራት የፕሮቴስታንት ዲኖሚሽን እንዴት መሠረቱን ሊጥል እንደቻለና መስራቾቹንም በጥቂቱ ተመልክተናል። በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው የ16ኛ ክፍለ ዘመን የሉተር፣ ካልቪንና ዚዊግሊን እንዲሁም የተለያዩ መናፍቃን አገዘመሩ በከፍተኛ ደረጃ መብቀሉንና መጽሐፍ ቅዱስን ማንም መተርጐም ይችላል የሚለው ትምህርት ምን ያህል የተዛባ አመለካከትን ፈጥሮ ቁጥራቸው የበዛ መናፍቃን እንዲፈጠሩ ማድረጉን ነው። እነዚህን የእምነት ድርጅቶች ትምህርታቸውን፣ መስራቹን፣ የት እንደተመሰረቱና አሁን የት እንደሚገኙ በዝርዝር አስቀድመን ከመመልከታችን በፊት ለሚቀጥሉት የኑፋቄ ትምህርት በመነሻነት ምክንያት የሆኑትን ሁለት መሠረታዊ ምክንያቶችን እንቃኛለን።

### 5.1 መሰረታዊ መነሻ ምክንያት

በዚህ ክፍለ ዘመን የስህተት ትምህርቶች ፊር ለቀው ሊወጡ የቻሉት በወቅቱ በከፍተኛ ሁኔታ ተነስተው በነበሩ ሁለት አመለካከቶች ምክንያት ነበር።

**አንደኛ፡-**

የመጀመሪያው ምክንያት ለዘብተኛ አመለካከት ተብሎ ይጠራል። የተጀመረ ለዘብተኝነት ከ1724-1804 በኑአማኑኤል ካንት (Emmanuel Kant) የተጀመረ ሲሆን፣ በለዘብተኝነት የተነሱት ሃሳቦች የሚከተሉት ናቸው።



www.ethiopianorthodox.org

ሀ) ለሰብአዊ አመክንዮና ለልምድ ትኩረት መስጠት (ሁሉ ነገር በምክንያታዊነትና በልምምድ መታወቅን ያስተምራሉ።)

ለ) ሃይማኖታዊ እምነቶች በሰው የአስተሳሰብ ሚዛንነትና እንዲሁም በሳይንሳዊ መፈተን አለባቸው ይላሉ። ይህም መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር የሚነግረን መርመርና በሳይንስ መረጋገጥ አለበት ይሉ ነበር።

ሐ) መጽሐፍ ቅዱስ ስህተት አልባነት አይቀበሉም። ይህንን ሲያብራሩ "መጽሐፉ የሌሎች ሰዎች ልምምድ ሪፖርት ነው። መጽሐፉ አርአያነትን ያሳያል እንጂ የሕይወት ምግብነት የለውም ስለዚህ በስህተት የተሞላ ነው" ይላሉ።

መ) በተፈጥሮአዊ (በፍጡር)ና በልዕለ ተፈጥሮ (Super natural) ማለት በፈጣሪ መካከል ልዩነት የለም ይላሉ። ይህንን ሲያብራሩ በአምላክና በሰው፣ በክርስቶስና በሰው ልዩነት የለም በማለት ያስተምራሉ።

ይህ ትምህርት ፐንታይዝም (Pantheism) ይባላል። የፓንታይዝም ክህደት "እግዚአብሔር ሰብአዊነት (አካል) ያለው ሳይሆን በፍጥረት የሚገኙትን ኃይላትና ሕጎችን የሚያጠቃልል ነገር ነው።" ይላል። ይህ አመለካከት በሁሉም ፍጥረት ውስጥ እግዚአብሔር አለ ፍጡርም እግዚአብሔርነት አለው ማለት ነው።

ክርስቲያን ሳይንስ (Christian Science) ይህንን ትምህርት የሚዲያ ሽፋን ሰጥቶት በBBC እያሰራጨ ያለ ሲሆን እግዚአብሔርነት አለን ኢየሱስንም መሆን እንችላለን የሚሉ ትምህርቶችን እየሰጠ ነው።



## ሁለተኛው፡-

ይህ አመለካከት አዲስ ቀጥተኛ ሃይማኖት የሚባል ሲሆን ይህ አመለካከት የክርስትና ሃይማኖት መሰረትና የእምነት፡ መመሪያ የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስን ማጣጣልና ከጥቅም ውጭ ማድረግ ዓላማው የነበረ እንቅስቃሴ ነው። በዚህ መሠረት ስለመጽሐፍ ቅዱስ የሚከተለውን ይክዳሉ፡-

ሀ) መጽሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ ሃሣብ የለውም፤

ለ) እንደ ክርስቶስ ትንሣኤ ያሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አፈ ታሪክ ናቸው።

ሐ) የመጽሐፍ ቅዱስ አብዛኛው ክፍል በአፈ ታሪክ የተሞላ ነው የሚሉ ክህደቶች ናቸው።

እነዚህ ሁለት ተዕዕኖዎች ፈር የለቀቀ የኑፋቄ ትምህርቶች በየጊዜው እንዲነሱ መሰረት ሆነዋል። በመቀጠል የምንመለከታቸው የኑፋቄ ትምህርቶች የእነዚህን መሠረት የያዙ ናቸው።

በዚህ ተዕዕኖ ውስጥ የሚከተሉትን እናገኛቸዋለን።

## ፕሮቴስታንቲዝም

ፕሮቴስታንቲዝም እንቅስቃሴ የተጀመረው በሉተር አስተምሮ መሠረት ቢሆንም ቀድመው ብዙ እንቅስቃሴዎች 14ኛ ክ/ዘመን ጀምሮ እንደነበር ታሪክ ያመለክታል።

ፕሮቴስታንት ማለት ተቃውሞ የተለየ ማለት ነው። በመሆኑም የፕሮቴስታንትን በአመለካከት ምሁራን በሶስት ይከፍሏቸዋል።



www.ethiopianorthodox.org

የብልፅግና ወንጌል ሰባኪዎች እውነተኛው የክርስቶስ ቃል ስላለቀባቸው የሚከተለውን ፈጠራ ይናገራሉ።

- "ኢየሱስ ሀብታም (ከበርቴ) ነበር። ይሁዳ ሲሰርቀው እንኳን አያውቅም ይላሉ።" ይሁንና በወንጌል እንደ ተገፈው፦ በከብቶች በረት የተወለደው፣ በአናጢው በዮሴፍ ቤት ያደገው፣ ለቀበሮዎችና ለወፎች ቤት አላቸው የሰው ልጅ (ወልደ እጓለ እመሕያው) እራሱን የሚያስጠጋበት የለውም እያለ ያስተማረውን ጌታ ከበርቴ ማለት የሰይጣን ትምህርት ነው (ማቴ. 8፥20 ይመልከቱ)።

- "በእግዚአብሔር ተስፋ መስረት መጨነቅ ብቻ አይደለም ኃጢያት፣ ድህነትም ኃጢያት ነው።" ይላሉ (Not only is worrying a sin, but being poor is a sin, when God promises prosperity)

ይህ የዘራፊዎችና የሆዳሞች በደህም ገንዘብ የሚንደላቀቁ ሰዎች ቋንቋ ነው። ጌታ ግን "የሰው ህይወቱ በገንዘብ ብዛት አይደለም" ሲል ድህነት ኃጢያት ነው የሚሉትን ያሳፍራቸዋል (ሉቃ.12፥16-21)። ቅዱስ ጳውሎስም "ገንዘብን መወደድ የኃጢያት ሁሉ ስርነው" ይለናል 1ጢሞ.6፥9-10 ክርስቲያን በገዛ ላቡ እየሰራ ዋጋውን ያገኛል እንጂ አታሎ አይዘርፍም ሀዋርያው "...በገዛ እጃችን እየሰራን እንደክማለን" 1ቆሮ. 4፥12 ይላል። በወንጌል "አንተ ደሃ" ብሎ ሰዎችን ጌታ ሲያርቅ፣ ሲንቅ አልተመለከትንም ይልቁን ምስኪኖችን የፍቅሩን ምግብ እንዲበሉ እንዲረኩም ሲያረድ እናያለን እንጂ።

"እግዚአብሔር የሚፈልገው አማኞች ከድህነት ብቻ አርነት እንዲወጡ አይደለም፤ ልጆቹ ምርጥ ምግብ እንዲበሉ፣ ምርጥ



የሆነውን እንዲለብሱ፣ ምርጥ መኪና እንዲያሽከረክሩ፣ የሁሉም ምርጥ የሆነ ኑሮ እንዲኖሩ ነው። (God not only wants to deliver believers from Poverty, He wants his children to eat best, He wants them to wear the best clothing, He wants them to drive the best cars, He wants them to have a best of everything- A different Gospel p988 p.175)" ይላሉ።

የእግዚአብሔር ተቀዳሚ አላማ ግን ይህ አይደለም፦ መንግሥቱን የምንወርስበት እምነት እንዲኖረን ነው። "የእግዚአብሔርን መንግሥት ፈልጉ..." እንደተባለ ማቴ. 7፥33። የአባቶቻችን ህይወትም ኑሮ ይህንኑ ነው የሚያሳየን። ለሥጋ ምቾት ቦታ ሳይሰጡ ለክርስቶስ ወንጌል ደከሙ "ለዓለም ለመላዕክትም ለሰዎችም መጫወቻ ሆነናል እግዚአብሔር እኛን ሐዋርያቱን ሞት እንደ ተፈረደባቸው ከሰዎች ከሁሉ ይልቅ የኋላኞ እንዳደረግን ይመስለኛልና... እስከዚህ ሰዓት ድረስ እንረባለን፣ እንጠማለን፣ እንራቆታለን፣ እንጎሰማለን፣ እንከራተታለን፣ በገዛ እጃችን እየሰራን እንደክማለን" (2ቆሮ. 8፥9)። ሲል ሃዋርያው ተናግሯል። ለሚከተሏቸው ክርስቲያኖች በቃልም በግብርም የማያስተምሩት ሥጋንና ክፉ መሻቱን አሸንፈው መስቀሉን እንዲሸከሙ ነው "የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑት ሥጋን ከክፉ መሻቱና ምኞቱ ጋር ሰቀሉ" ገላ. 5፥24።

ቅዱሳን አባቶቻችን የዚህን ዓለም ጠፊነትና ኃላፊነት የሰውንም ዘመን ከንቱነት ተረድተው ህይወታቸውን ለዘላለም ለክርስቶስ ሊያስገዙ ያላቸውን ሁሉ ትተው ተከተሉ እንጂ ለሌላ ትርፍ ነገር



www.ethiopianorthodox.org

1. ወንጌላውያን (Evangelical)
2. ዳግም አጥማቂዎች (አናባብቲስት)
3. ካርዚማቲክ (New Pentecost cal)

## 1. <u>ወንጌላውያን</u>

ወንጌላውያን የሚባሉት እንደማንኛውም የፕሮቴስታንት ዲኖሚኔሽን የሉተርን ያልተለወጠውን የኦስበርግ የሃይማኖት መግለጫ የሚቀበሉ ሲሆን፣ የሕፃናትን ጥምቀት ይቀበላሉ፣ በልሳን መናገርን፣ በመንፈስ መሞላትን አይቀበሉም። እንዲሁም የአዲሱ የጴንጤቆስጤ እንቅስቃሴን ይቃወማሉ። በሀገራችን ወንጌላውያን በሚል የሚጠሩት መካነ ኢየሱስ ነው።

## 2. <u>መጥምቃውያን</u>

መጥምቃውያን አናባብቲስት ይባላሉ ዳግም አጥማቂዎች ማለት ነው። ከሌላ የክርስትና እምነት ወደድርጅታቸው የሰበኩትና የወሰዱትን ደግመው ያጠምቃሉ። እነዚህ የሕፃናትን ጥምቀት አይቀበሉም። ሕፃናት የቤተክርስቲያን አካል አይደሉም ይላሉ። አስቀድሞ መመረጥን (ፋሬዘላደይን) ያስተምራሉ። በመንፈስ መጠመቅ በማለት በመንፈስ ሙሴት ላይ አፅንኦት ይሠጣሉ። በመንፈስ መሞላትና በልሳን መናገር አማኙ ለመዳኑ ማረጋገጫ ነው ይላሉ። እንደ ሙሉ ወንጌል፣ አማኑኤል ባብቲስ የዚህ ክፍል ናቸው።



## 3. <u>ካርዚማቲክ (አዲስ ጴንጤቆስጤ እምነት)</u>

አዲሱ የጴንጤቆስጤ አመለካከት በመሰረታዊው ታሪክ ከ1930 ጀምሮ እንቅስቃሴውን የጀመረ ሲሆን እንደማንኛውም የፕሮቴስታንት የእምነት ድርጅት ሆኖ የሚከተሉትን በአምልኮ ቦታቸው አጥብቀው ይፈጽሟቸዋል።

- በመንፈስ መሞላትና በልሳን መናገር በጠነከረ መልኩ ይፈፀማል።
- በመንፈስ መገደንስ (Sling with sprit)፤ ይህም መንፈስ ቅዱስ ገነደሰን እያሉ በየአዳራሹ እርቃንን መዘረር ነው።
- በመንፈስ መሳቅ (Laughing with Sprit) ከመጠን በላይ ተንተክትኮ መሳቅና ማወክን ያመለክታል።
- ለክርስቶ መሳሳም /ይህም በክርስቶስ ተሳሳሙ በሚባል ጊዜ ሁሉም ያገኘውን ይስማል/፡
- በመንፈስ መደነስ (Dancing with sprit) መንፈስ ቅዱስ ያስደንሳል በማለት ራፕን፣ ሬጌን፣ እንክትክት እያሉ መደነስን ማዘውተር።
- የብልፅግና ወንጌልን (Prosperity Gospel) ማስፋፋት ናቸው።

## <u>የብልጽግና ወንጌል ምንድነው? /Prosperity Gospel/</u>

የብልጽግና ወንጌል አስተማሪዎች "ድህነት የክፋት ሁሉ ስር ነው፤ ድህነት ወንበዴ ነው፤ ድህነት የኃጢያት በር ነው ፤ አባታችን ባለፀጋ ነው፤ ባለፀጋ ልጆች ነው የወለደው... መስጠት (ገንዘብን) ከኢየሱስ ስም የበለጠ የመገሰፅ ኃይል አለው" ይላሉ። ይሁንና በክርስትና ገንዘብ ወይም ሀብት የጽድቅ ምልክት አይደለም። ለክርስቲያን ትልቁ ሀብቱ የእግዚአብሔር ክንድ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

የብልፅግና ወንጌል ሰባኪዎች እውነተኛው የክርስቶስ ቃል ስላለቀባቸው የሚከተለውን ፈጠራ ይናገራሉ።

- "ኢየሱስ ሀብታም (ከበርቴ) ነበር። ይሁዳ ሲሰርቀው እንኳን አያውቅም ይላሉ።" ይሁንና በወንጌል እንደ ተፃፈው፡- በከብቶች በረት የተወለደው፣ በእናቱም በዮሴፍ ቤት ያደገው፣ ለቀበሮዎችና ለወፎች ቤት አላቸው የሰው ልጅ (ወልደ እጓለመሕያው) እራሱን የሚያስጠጋበት የለውም እያለ ያስተማረውን ጌታ ከበርቴ ማለት የሰይጣን ትምህርት ነው (ማቴ. 8፥20 ይመልከቱ)።

- "በእግዚአብሔር ተስፋ መስረት መጨነቅ ብቻ አይደለም ኃጢአት፣ ድህነትም ኃጢአት ነው።" ይላሉ (Not only is worrying a sin. but being poor is a sin. when God promises prosperity)

ይህ የዘራፊዎችና የሆዳሞች በደሀም ገንዘብ የሚንደላቀቁ ሰዎች ቋንቋ ነው። ጌታ ግን "የሰው ህይወቱ በገንዘብ ብዛት አይደለም" ሲል ድህነት ኃጢአት ነው የሚሉትን ያሳፍራቸዋል (ሉቃ.12፥16-21)። ቅዱስ ጳውሎስም "ገንዘብን መውደድ የኃጢአት ሁሉ ስር ነው" ይለናል 1ጢሞ.6፥9-10 ክርስቲያን በገዛ ላቡ እየሰራ ዋጋውን ያገኛል እንጂ አታሎ አይዘርፍም ሀዋርያው "...በገዛ እጃችን እየሰራን እንደክማለን" 1ቆሮ. 4፥12 ይላል። በወንጌል "አንተ ደሃ" ብሎ ሰዎችን ጌታ ሲያርቅ፣ ሲንቅ አልተመለከትንም ይልቁን ምስኪኖችን የናቁትን ምግብ እንዲበሉ እንዲረኩም ሲያረድ እናያለን እንጂ።

"እግዚአብሔር የሚፈልገው አማኞች ከድህነት ብቻ አርነት እንዲወጡ አይደለም፣ ልጆቹ ምርጥ ምግብ እንዲበሉ፣ ምርጥ



የሆነውን እንዲለብሱ፣ ምርጥ መኪና እንዲያሽከረክሩ፣ የሁሉም ምርጥ የሆነ ኑሮ እንዲኖሩ ነው። (God not only wants to deliver believers from Poverty, He wants his children to eat best. He wants them to wear the best clothing. He wants them to drive the best cars. He wants them to have a best of everything- A different Gospel p988 p.175)" ይላሉ።

የእግዚአብሔር ተቀዳሚ አላማ ግን ይህ አይደለም፡- መንግሥቱን የምንወርስበት እምነት እንዲኖረን ነው። "የእግዚአብሔርን መንግሥት ፈልጉ..." እንደተባለ ማቴ. 7፥33። የአባቶቻችን ህይወትም ኑሮ ይህንኑ ነው የሚያሳየን። ለሥጋ ምቾት ቦታ ሳይሰጡ ለክርስቶስ ወንጌል ይከፍሉ "ለዓለም ለመላዕክትም ለሰዎችም መጫወቻ ሆነናል እግዚአብሔር እኛን ሐዋርያቱን ሞት እንደ ተፈረደባቸው ከሰዎች ከሁሉ ይልቅ የኋለኛ እንዳደረገን ይመስለኛልና... እስከዚህ ሰዓት ድረስ እንራባለን፣ እንጠማለን፣ እንራቆታለን፣ እንጎሰማለን፣ እንከራተታለን፣ በገዛ እጃችን እየሰራን እንደክማለን" (2ቆሮ. 8፥9)። ሲል ሃዋርያው ተናግሯል። ለሚከተሏቸው ክርስቲያኖች በቃልም በግብርም የሚያስተምሩት ሥጋንና ክፉ መሻቱን አሸንፈው መስቀሉን እንዲሸከሙ ነው "የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑት ሥጋን ከክፉ መሻቱና ምኞቱ ጋር ሰቀሉ" ገላ. 5፥24።

ቅዱሳን አባቶቻችን የዚህን ዓለም ጠፊነትና ኃላፊነት የሰውንም ዘመን ከንቱነት ተረድተው ህይወታቸውን ለዘላለም ለክርስቶስ ሲያስገዙ ያላቸውን ሁሉ ትተው ተከተሉ እንጂ ለሌላ ትርፍ ነገር



www.ethiopianorthodox.org

አልሠሩም ሁሴ "...በእውነት ሰው እንደ ጥላ ነው፤ ያከማቻል፣ የሚሰበስብለትን አያውቅም" የሚለውን ቃል ያዘክራሉ። ለእምነት ልጆቻቸውም "...አካሔዳችሁ ገንዘብን ያለመውደድ ይሁን ያላችሁ ይብቃችሁ" ይላሉ እንጂ ለተለያየ የዘረፋና የብልፅግና ስልት እራሳቸውን አያዘጋጁም ነበር (መዝ. 38(39)፥6፣ ዕብ. 13፥5)።

ለማጠቃለል ድህነት ኃጢያት አይደለም፣ ጽድቅም ድህነት ብቻ አይደለም። ባለጠግነት ኃጢያት፣ ብልጽግና ጽድቅ አይደለም። የእግዚአብሔር ፍርድ በእነዚህ የተመሰረተ አይደለም። ዕድቁና ኃጢያቱ ግለሰቡ (ክርስቲያን) በሚኖረው ኃይማኖታዊ ሥራ ላይ ነው የሚገለጠው።

እንግዲህ ካርዝማቲኮች ከዚህ ውጭ ፈውስን የመፈለግና መስበክ፣ የእምነት ቃል (Word faith) ማለትም ተመኝ ይሆንልሃል ይህም ሀሎት ቤት ሆነህ አዲስ መኪና ተመኝተህ ሀልዩ ውጭ ታገኘዋለህ የሚሉ ፈሆችን ያስተምራሉ። በሀገራችን የአሸናፊዎች መቅደስ (Winner Chapel) የተሰኘው ድርጅት ይህንን በ1992-93 አጥብቆ ያስተምርና ትራክት ሁሉ ይበትን እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው።

እነዚህን ጠቀስን እንጂ እጅግ ብዙ አይነት አዳዲስ ትምህርቶች በየእለቱ በመናፍቃኑ እየተዘሩ መሆኑን ልብ ሊባል ይገባል። በዚህ ምድብ ውስጥ የሚካተቱ ድርጅቶች

- የክርስቶስ ወታደር /Army Faith/
- የአሸናፊዎች ቤተመቅደስ /Winner Chapel/
- ፅዮን ቤተክርስቲያን /Zion Church/
- የእግዚአብሔር ጉባኤ /Assembly of God/



- መኸር ቤተክርስቲያን /Harvest Church/
- ቀራንዮ የወንጌል አገልግሎትና የመሳሰሉት ናቸው።

ለአጠቃላይ ግንዛቤ በሶስት ክፍል የተመለከትናቸው የፕሮቴስታንቲዝም የሚከተሉትን በዋናኛነት ይዘው ያስተምራሉ።

1. •66ቱን መጽሐፍ ብቻ ይቀበላሉ ትውፊትንና የአባቶችን የሃይማኖት ቀኖና አይቀበሉም። (መካነ ኢየሱስ ብቻ ትቀበላለች።)
2. ለመዳን እምነት እንጂ ሥራ አያስፈልግም ይላሉ።
3. በሥልጣነ ክህነት አያምኑም ምስጢሩን አይቀበሉትም።
4. የጥምቀት ትምህርታቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። ይኸውም አንድ ሰው መጠመቁ ለማመኑ ምልክት ነው (Symbol) እንጅ ጥምቀቱ አያድነውም ይላሉ። አብዛኛዎቹም የሕፃናትን ጥምቀት አይቀበሉም።
5. በጌታ እራት ብለው በሚጠሩት በሥጋወደሙ ላይ ሁለት አይነት አመለካከት አላቸው። አንደኞቹ በቀጥታ መታሰቢያ (Rembrance) ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ ክርስቶስ በሕብስቱና በወይኑ ላይና ታች ይገኛል እንጂ አይለወጥም ይላሉ።
6. ለሞቱ ሰዎች መጸለይ በቅዱሳን ስም ምልጃ ማቅረብን ይክዳሉ።
7. የወላዲተ አምላክን ዘላለማዊ ድንግልና ይክዳሉ፤ አማላጅነቷንም አያምኑም።
8. በመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ላይ አብዛኛው ፕሮቴስታንት የስህተት ትምህርት ያስተምራሉ።
9. ኢየሱስ በአሁኑ ግዜ ይጸልይልናል (ያማልዳል) ይላሉ።



www.ethiopianorthodox.org

እነዚህ በመጠኑ የተመለከትናቸው ነገር ግን ሰፊና ብዙ ዘርፍ ያለው የስህተት ትምህርቶች ናቸው።

## 5.2 የሐዋርያት እምነት ድርጅት (Only Jesus)

### 1. አመሰራረቱ

ይህ የስህተት ትምህርት ከእግዚአብሔር ጉባኤ ወይም (Assembly of God) በ1950 ተገንጥሎ የወጣ ጴንጤቆስጣዊ እምነትን የሚያራምድ ሆኖ በሥላሴ የማያምን ነው።

የተመሰረተው በአሜሪካን ነው። በአሁኑ ግዜ በካሊፎርኒያ ትልቁ ኮሌጅና የድርጅት ቦታቸው ሲሆን ኮሌጁ Christian Life College ይባላል። በሀገራችን ግን የተመሰረተው በ1956 አካባቢ የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን ከሚባል ከአሜሪካን ሀገር በመጡት ሚሲዮኖች አማካኝነት ተ/ማርያም የተባለው ሰው እንደመሰረተው ይታመናል።

ትምህርተ ክህደታቸውም የሚከተሉት ናቸው።

#### ሀ. ስለእግዚአብሔር

በሥላሴ አያምኑም ትምህርታቸውም ፍፁም ሰባልዮሳዊ ነው (አንዱ እግዚአብሔር በተለያየ ግዜ በሶስት ቅርፅ እራሱን ገለጠ የሚለው ነው።)

#### ለ. ስለ ክርስቶስ

ስለ ክርስቶስ የሚያስተምሩት ትምህርት እንደሚከተለው ነው "እግዚአብሔር አምላክ በሥጋ አይን ሳይታይ መንፈስ ሆኖ ይኖር ነበር።



ነገር ግን በኋላ ቃሉን (ዝርው ቃል ነው) ሥጋ እንዲሆን አደረገው ማለትም ኢየሱስ በተባለው ሰው ውስጥ አደረ" በማለት የክህደት ቃልን ያስተምራሉ።

#### ሐ. ስለመንፈስ ቅዱስ

ስለመንፈስ ቅዱስ ደግሞ እንዲህ ይላሉ "መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስ ከተባለው ሰው ውስጥ ያደረው አምላክ ከሚወጣ እስትንፋስ ነው።" ይላሉ።

#### መ. ስለ ጥምቀት

በማቴዎስ ወንጌል 28፥19 የተጠቀሰውን የጌታን ትምህርት በመካድ በኢየሱስ ስም ብቻ ብለው ያጠምቃሉ።

ከዚህ ውጭ ሙሉ ለሙሉ የፕሮቴስታንት ጴንጤቆስጣውያን የሚያምኑትን የምናሉ። በተለይም በመንፈስ መሞላትና በልሳን መናገር በስብሰባ ቦታቸው ፍፁም እብደትን በሚመስል መልኩ በማጓራት ይፈጽማሉ።

## 5.3 ሞርሞኒዚም

የኋለኛው ዘመን ቅዱሳን የክርስቶስ ቤተክርስቲያን

ይህ እምነት The later days of saints of Church of Jesus Christ ተብሎ ይጠራል።



www.ethiopianorthodox.org

## አመሰራረቱ

የዚህ እምነት ድርጅት መስራች ጆሴፍ ስሚዝ ጁኦር ይባላል። የተወለደው ታህሳስ 23 ቀን 1805 በሀገረ አሜሪካን ቫራን ቬር ሞት በተባለ ስፍራ ነው። እምነቱን በ1830 በኒዮርክ የመሰረተው ሲሆን አሁን ዋናው መስሪያ ቤት በስልት ሌት ሲቲ ይገኛል (አሜሪካ)

ጆሴፍ ስሚዝ እምነቱን ሊመሠረት የቻለው ራእይ ተመልክቶ እንደሆነ ራእዩን ሞርሞን የተባለ ሰው እንዳሳየውና የተለያዩ የእምነቱን መመሪያዎች እንደተቀበለ ይናገራል።

## የእምነቱ ትምህርተ ክህደት

### ሀ) ስለ እግዚአብሔር

ሞርሞኒዝም እራሱን የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ቤተክርስቲያን ብሎ ቢጠራም ትምህርቱ ግን ፍጹም ሰይጣናዊ ፍልስፍና ነው። ስለእግዚአብሔር አብ "በአንድ ወቅት ሰው ነበር ነገር ግን አምላክ ሆነ ሚስቱም እመ ሰማይ ትባላለች። እርሱም (አብ) ሥጋዊ አካል አለው ይላል። በሥላሴ አያምኑም ይልቁን የሦስት መለኮት ትምህርት ያስተምራሉ።"

### ለ) ስለ ክርስቶስ

እርሱ የሰዎችና የመንፈሳውያን ፍጡራን ታላቅ ወንድም ነው። የሰውነቱ መገኘት (ሥጋዌው) በአብና (ኤሎሔም) ማርያም ጋብቻ ነው ይላሉ። ስለምድራዊ አገልግሎቱ ትዳር ይዞ ነበር። በመስቀል መሰቀሉም ለትንሣኤ እንጂ ለድኅነት ጥቅም የለውም በማለት ክህደትን ያስተምራሉ።



### ሐ) ስለመንፈስ ቅዱስ

ሞርሞኖች መንፈስ ቅዱስን "እንደ ፈሳሽ ያለ ነገር ነው አገልግሎቱም አብ ስልጣኑን የሚያጠናክርበትና ሚያስፋፋበት ነው።" በማለት ብዙ ስፍራም አይሰጡትም።

### መ) ስለ እመቤታችን

የጠለቀ ትምህርት ባይኖርም እመ ሰማይ ወይም የኤሎሒም ሚስት ይሏታል።

### ሰ) ስለድኅነት

በሞርሞን እምነት የድኅነት ሀሣብ ወደ አምላክነት መለወጥ ወይም መድረስ ነው ብለው ያስተምራሉ። ድኅነት ለማግኘትም

- በድርጅቱ አምኖ የእጅ መጫን ስርዓትን መሳተፍ፤
- ለሞርሞን መታመንና ልዩ ጥምቀት መወስድ
- በተለየው ማምለኪያ ቦታቸው ለጠነከሩት ብቻ የሚወሰድ ቁርባን መቀበል ይገባል። (ቁርባኑን የማን እንደሚሉትና ከምን እንደሚዘጋጅ መረጃ የለም።)

### ረ) . ስለ መጽሐፍ ቅዱስ

ሞርሞኖች መጽሐፍ ቅዱስን በስህተት የተሞላ ነው። ትርጉሙ የሚቃናው በእኛ ሲዘጋጅ ብቻ ነው ይላሉ። የራሳቸውንም የመማሪያ መጽሐፍ በማዘጋጀት "አዲሱ ብርሃን" (The New light) ብለው ይጠሩታል። መጽሐፍ ቅዱስን ግን አሮጌው ብርሃን (The old light) ይሉታል።



www.ethiopianorthodox.org

ሸ) ክህነት

በሞርሞኖች (የኋለኛው ቀን ቅዱሳን) እምነት መሠረት የክህነት ሁኔታ አሮናዊና የሌዋውያንን ይዞታ የተከተለ መሆኑ ያስተምራሉ። ስለክህነታቸው የትመጣ ሲናገሩ "ሞሮናይ የተባለው መልአክ በ1827 ለስሚዝ ተገልጦለት የሞርሞንን መጽሐፍ ከሰጠው በኋላ ለክህነት ሹመት ደግሞ መጥምቁ ዮሐንስ በ1829 ከሌሎች አገልጋዮች ጋር ክህነት ሰጥቶታል። ክህነቱም አሮናዊ ነው" ብለው ያስተምራሉ። በሞርሞን እምነት የአፍሪካ ዝርያ ያላቸው ክህነት የማይፈቅድላቸው ሲሆን 1978 ወዲህ ግን ብቃታቸው እየታየ እንዲሰጥ ተወስኗል።

## 5.4 አለም አቀፍ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን (World wide Church of God)

ይህ ድርጅት ከዚህ ስያሜ ውጭ በመስራቹ ስም አርምስትሮንጊዝም ተብሎ ይጠራል።

### አመሰራረቱ

የመሰረተው ከ1892-1986 የኖረው ሔርባት ድብልዩ አርሞስትሮንግ ነው በ1934 ዓ.ም በታው ፍላደርፊያ አሜሪካን ነው።

### ትምህርተ ክህደት

ሀ) ስለሥላሴ

ከቤተክርስቲያን ትምህርት በወጣ መልኩ ስላሴን እንደ አንድ ቤተሰብ ኑሮ ነው፣ የሚመለከቱት ይህም በመበላለጥ ማዘዝ መታዘዝ እንዳለ ያስተምራሉ።



ለ) ስለ ክርስቶስ

"ኢየሱስ በሰው መልክ የተገለጠ አምላክ ነው" ትንሣኤውም በአካለ ሥጋ አይደለም። በምትሐት ነው ብለው ያስተምራሉ።

ሐ) ስለ መንፈስ ቅዱስ

መንፈስ ቅዱስን አካል የለውም እንደ ንፋስ ኃዝና የተለየ ኀይል ነው በለው ያምናሉ።

መ) ድኅነት

ድኅነት በጸጋ ብቻ ነው የሚገኝ የሚለውን እንደያዙ ነገር ግን የአይሁድ ልማድን መጠንቀቅ ለድኅነት ዋስትና ነው ይላሉ። በዚህም መሠረት የአይሁድን ሰንበት፣ በዓላቶቻቸውን፣ ያከብራሉ። ይህ ካልተጠበቀ ድኅነቱ ዋጋ የለውም ይላሉ።

ሠ) ስለ ሰው ተፈጥሮ፣ ስለ ሲዖል መኖር

አርምስትሮንጊዝም ሰው መለኮታዊነት አለው ብለው ያምናሉ። ነፍስ ሕያዊነት የላትም (ዘላለማዊነት) በዚህም መሠረት የቅጣት ሥፍራ የሆነት ሲኦልና የመላእክት የሉም የፈጠራ ስራዎች ናቸው ይላሉ።



www.ethiopianorthodox.org

## 5.5 ዩኒፊኬሽን ቸርች

### አመሰራረቱ

የዚህ እምነት መስራች የደቡብ ኮሪያ ተወላጅ ሰን ምያንግሙን ነው። ይህ ሰው ከ1925 አካባቢ በኮሪያ የተወለደ ሲሆን ይህንን እምነት በ1954 ዓ.ም. መሠረተው።

### ትምህረተ ክህደቱ

#### ሀ) ስለ ፈጣሪ

እምነቱ በስላሴ አያምንም ስለእግዚአብሔር ሲያስተምርም "እግዚአብሔር ከራሱ አካል ፍጥረተ ዓለምን ፈጠረ ፍጥረተ ዓለምም የእግዚአብሔር አካል ነው። ስለዚህ በሁሉም ፍጥረተ ዓለም ውስጥ እግዚአብሔርነት አለው" ብሎ ያስተምራል።

ዩኒፊኬሽን ቸርች "እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ አይደለም በዚህም ምክንያት መጭውን ጊዜያት አያውቅም ባለማወቁ ደግሞ እየተሰቃየ ነው" ይላሉ። እንግዲህ እንደ እምነቱ ትምህርት ሁሉን ማወቅ የተሳነው አምላክ ከዚህ ችግሩ ለመላቀቅ እንዲቻለው የወደፊቱን የሚያውቅ ሰውን ፈለገ። በዚህም የዚህ እምነት መስራች ሰን ምያንግሙን አገኘ ይላሉ። በዚህ እምነት መሰረት ሁሉን ማወቅ ከአምላክ ይልቅ ሰው አለው ይላሉ።

#### ለ) ስለክርስቶስ ያላቸው ትምህርት

ይህ እምነት ምንም እንኳን በክርስትናው ስም ቢነሳም ነገር ግን ምንም አይነት መመሳሰል የሌለው አጋንንታዊ የፈጠራ እምነት በመሆኑ



ስለክርስቶስ የሚያስተምረው በሙሉ ልብ ወለድና ፈጠራ ነው። እንዲህም እያሉ ይክዳሉ።

- ኢየሱስ አምላክ ሳይሆን ፍፁም ሰው ነው።
- የተወለደው ከድንግል ማርያም ሳይሆን ከዘካርያስ ነው።
- በዚህ ምድርም የመገለጡ ምስጢር የሰውን ልጅ ለነፍሱ ቤዛ ለመሆን ሳይሆን "የተበታተነውን የአይሁን ግዛት አንድ ለማድረግ ነው" ከዚህም ጋር
- የተዋበችና ፍፁም የሆነች ሙሽራን በዝናው ለማግኘት እና
- የተዋበ ቤተሰብን ለመመስረት ነበር። ነገር ግን ይህ ሁሉ አልተሳካለትም ሞተ ብለው ያስተምራሉ።
- የክርስቶስን በሥጋ መነሳት፣ ማረጉን ደግሞም መምጣቱን አይቀበሉም።

#### ሐ) ስለ መንፈስ ቅዱስ ያላቸው ትምህርት

ይህ የክህደት እምነት ስለመንፈስ ቅዱስ ብዙ ቦታ ባይሰጠውም ነገር ግን ያታውን ለይቶ በመስጠት "እንስት" ወይም "የሴትነት" ያታን ይሰጠዋል። ተግባሩም በመንፈሳዊ አለም (Spiritual world) ከኢየሱስ ጋር በመሆን ሰዎችን ወደ ሰን ምያንግ ያቀርባሉ ይመለምላሉ ብለው ያምናሉ።

#### መ) ስለ ድኅነት ያላቸው ትምህርት

ይህ እምነት በኢየሱስ ክርስቶስ ስለተገኘው መዳን ግድ አይሰጠውም። ነገር ግን ስለመዳን ስለኃጢአት እንዲህ ያስተምራሉ።



www.ethiopianorthodox.org

"እውነተኛውን የሰው ልጅ ሁሉ ወላጅና ወዳጅ የሆነትን ሙንና ሚስቱን ማመን (መቀበል) ነው" ይላሉ።

ሰ) **<u>ስለ ትንሣኤ</u>**

በዳግም ምፅዓት (በትንሳኤ ዘጉባኤ) ያላቸው ትምህርትም የፈጠራ ነው። ክርስቶስ የትንሣኤ ተልዕኮውን አጠናቆ ስለማይጨርስ የሚያጠናቅቃለት ሱን ሙን ያንግ ነው።

የትንሣኤም ነገር በገነት ወይም በልዩ ስፍራ ነፍሳት መኖር ሳይሆን የሰው ልጅ ወደመናፍስት ዓለም መሔድ ነው እንጂ መነሳት የለም ይላሉ።

ረ) **<u>የቁርባን ስርዓታቸው</u>**

ይህ የእምነት ድርጅት ቁርባን በማለት ለአማኞች የሚያቀርበውና የሚቀበሉት 21 (ሃያ አንድ) ንጥረ ነገር የያዘና ከእነዚህ የተቀመመ ልዩ ወይን ነው። ወይኑን በሚጠጡ ወቅት የሙንና የስን ደም አለበት በማለት አምነው ይቀበላሉ። አጋንንት በዚህ የፈጠራ ግብሩ ሰዎችን እያሳተ ይገኛል።

ሠ) **<u>መጽሐፍትን በሚመለከት</u>**

የሕይወት ምግብ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ እምነት ስፍራ የለውም። ከመጽሐፍ ቅዱስ ይልቅ የእምነቱ መስራች የፃፈውን መጽሐፍ ይመሩበታል። መጻሕፍቶቹም "መለኮታዊ መርሐ" "እውነተኛው ፍፁም ኪዳን" የሚሉ መጠሪያ አላቸው። የመጻሕፍቱም አጠቃላይ ይዘት ስለእምነቱ መስራች የሚያትቱ ናቸው።



## <u>መጠቃለያ</u>

ዩኒፊኬሽን ቸርች ከመናፍስት ዓለም ጋር መገናኘትንና ሕብረት ማድረግን ያበረታታል። እንዲሁም በተለያዩ ዘር መሠረት ላይ ያተኮረ የሕብረት ጋብቻን ይፈፅማሉ። በቅርቡ 30,000 ጥንድ ጋብቻ በኮሪያ ተፈፅሞ ነበር። ጋብቻውን ሙን እንደባረከው ያምናሉ ያስተምራሉም።

## 5.6 <u>ዩኒቲ ስኩል ኦፍ ክርስቲያን</u>

የዚህ እምነት መስራቶች በአሜሪካን ሀገር በዩኒቲ መንደር 1845-1948 የተንቀሳቀሱት ሁለት መናፍቃን ናቸው። እነርሱም ቻርለስ ፊልሞርና ሚርትል ፊልሞር ናቸው። በመጀመሪያ እምነቱ የተመሠረተው በካንሰስ ሲሆን መስራቾቹም የፕሮቴስታን ክፍል ከሆነው የፕሬስቤቴሪያን እምነት ውስጥ ያምኑ ነበር።

### <u>ትምህርተ ክህደታቸው</u>

ሀ) **<u>ስለፈጣሪ</u>**

የክርስትናው መሠረት የሆነውን በስላሴ ማመንን አይቀበሉም። እንዲሁም ስለእግዚአብሔር አካልነት በመካድ የማይታይ ኃይል (Supper natural) ነው ይላሉ። እግአብሔር (God) ብለው ከመጥርት ይልቅ

- መርሐ (Principle)
- ሕግ (Low)
- ህልውና
- ሐሳብ (Thought)
- መንፈስ (Sprit) ይሉታል



www.ethiopianorthodox.org

ስለህልውናው ሲያስተምሩም ነፍስ በሥጋ ውስጥ እንዳለች ሁሉ እግዚአብሔርም በሁሉ ነገሮች ውስጥ ይገኛል ይላሉ። በዚህም መሠረት እምነቱ የመንፈስን ነገር እንጂ የአካልን ነገር አያምንም። አማናዊት ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔርን ሕልውና ስትናገር በሁሉ ስፍራ ይገኛል እንጂ በሁሉም ነገሮች ውስጥ አለ አትልም።

## ለ) ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ

እምነቱ እንደ ህድረት (Adoption) አስተማሪዎችና እንደ ሁለት ባህርይ ሁለት አካል አማኞች ኢየሱስና ክርስቶስን ለያይተው ያያሉ። በዚህም መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ አልነበረም ነገር ግን ሰው ነው። ሰይጣን ይህንን ትህርት የሚያስጠው አምልኮተ እግዚአብሔርን ለመቀነስና ወደ ብዙ አማልክት መንገድ ሰውን ለመምራት ነው። እንዲሁም በሥጋ የተገለጠውን የእግዚአብሔር ልጅን ሥራ ከንቱ ለማድረግ ነው።

በምድር ላይ የተሻለና የተለየ ተዓምራት ማድረጉ "የክርስቶስ አእምሮ" ስለነበረው ነው ይለሉ።

ክርስቶስስ ማን ነው የሚለውን ሲመልስ "ክርስቶስ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው ሳይሆን በሁሉም ሰው ውስጥ የሚገኝ ፍፁምነት ነው" ይላሉ።

## ሐ) ድኅነት/Salivation

ስለ ድኅነት ይህ የክህደት እምነት ሲያስተምር፥ "በክርስቶስ ማመን ድኅነት አያስጥም ይልቁንም ድኅነት ለማግኘት ኢየሱስ እራሱ



በኖረበት ዘመን ይፈልግ ነበር። ለማንኛውም ሰው ኃጢአት መስዋዕትም አልሆነም። አልሞተምም ለሰው ለመዳኑ የሚያስፈልጉትና ፍፁም የሚሆነው ክፋት፣ ዲያብሎስ፣ ኃጢአት፣ ድህነት፣ እርጅና አለመኖሩን ማመን እንዲሁም ሰው ሁሉ ከኢየሱስ የማይተናነስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ማመንና የእምነቱን የተለያዩ አስተምሮዎች መቀበል ፍፁም ያደርጉታል ይላሉ። ይህንን የማያውቅ ግን እንደገና እየተፈጠረ (Rebirth) ይኖራል ብለው ያስተምራሉ።

## መ) ስለሰው ልጅ፣ ስለ ሞትና የቅጣት ስፍራ

የሰው ልጅ ሞት የለበትም። ስለሞት የሚያስቡ ሰዎችም በተሳሳተ መረዳት ውስጥ ያሉ ናቸው። ነገር ግን ሰው "እስኪበራለት" ወይም "ፍፁም" እስኪሆን ድረስ ወደተለያየ አካል ውስጥ ይገባል። ይህንን የእምነት ስርዓት ወይም ሒደት ሰዎች ሞት ይሉታል እንጂ ሞት የለም ብለው ያስተምራሉ።

እንዲሁም በሰማይ አለ የሚባሉት ገነት ሲኦል መንግሥተ ሰማያት፣ ገሀነም እሳት ወዘተ የፈጠራ ወሬዎች ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ይህ ትምህርት የለም ይላሉ። ስለዚህም ሰው ስለሞት መጨነቅ፣ ስለኃጢያት መስራት አለመስራት ወዘተ መጨነቅ የለበትም፤ እንደሻው መኖር ይችላል ብለው ያስክዳሉ። የሰው ልጅ በእምነትና በምግባር ተጠብቆ ከመኖር እንዲቆጠብና አመፀኝነትን ዓለምን እንዲገዛና ፀያፍና አሳፋሪ በሆኑ የኃጢአት ግብሮች ትውልዱ እንዲያዙ ያበረታታሉ። በዚህም ምክንያት ዓለማችን እጅግ በረከሱ ሰዎች እየተሞላች ነው። አመፀኞችም ተዘክሮ ሞትን ዘንግተው እንደኖህ ዘመን እየኖሩ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

### ሰ) <u>ስለ ቅዱስ መጽሐፍ</u>

ይህ የክህደት እምነት ለክህደቱ ሃሳቦችና ለድርጅቱ መርሖዎች እንዲረዳት በዋነኛነት የማሳሳቻ መጽሐፍ ያዘጋጀ ሲሆን እርሱም "የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት" ብለው ሰይመውታል (ይህ መጽሐፍ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር የሚያሳትመው አይደለም) መጽሐፉ በምክንያታዊነት (Reason) ላይ የተመሠረተ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስን እንጠቀማለን ክርስቲያን ነን ቢሉም በመጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ እምነት የላቸውም። መጽሐፍ ቅዱስን ለተሰወሩ ነገሮች መፍትሔ የሚሰጥ የፍች ወይም የመተርጐሚያና የማጣቀሻ መጽሐፍ ነው ይላሉ። የክህደት ትምህርቱ ዓላማ ተዘክሮ ሞትን ፈፊ... እግዚአብሔርን ማጥፋት ነው።

## 5.7 <u>ስፕሪቲዝም (Spiritualism)</u>

### <u>አመሰራረቱ</u>

የዚህ እምነት መስራቾች ማርጋሬት እና ካቴና ፍክስ የተባሉ እህትማማቾች ናቸው። በ1840-50 አካባቢ በኒውዮርክ እምነቱን መስርተው መስበክና ማስፋፋት ጀመሩ። ይህ ድርጅት በይፋ በአሁን ጊዜ ጽ/ቤቱ ባይታወቅም ነገር ግን ብዙ ትንንሽ ቡድኖች (ክፍልፋዮች) አሉት።

### <u>ትምህርተ ክህደታቸውም</u>

### ሀ) <u>ስለፈጣሪ</u>

በሥላሴ ማመንን ይክዳሉ። እግዚአብሔርንም ምንድ ነው ለሚለው ምላሽ ሲሰጡ "ወሰን የሌለው የማሰብ ችሎታ ነው በተለየ አካሉ የሚ...



አይደለም ነገር ግን በተለየ የማሰብ ኃይሉ አለምን ይምራል እንጂ" ብለው ያስተምራሉ።

### ለ) <u>ስለ ክርስቶስ</u>

ስለ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚከተለውን ክህደት ያስተምራሉ "በምድር ላይ በነበረ ግዜ እንደ ነቢይ የሚታይ በአስተሳሰቡም የመጠቀ ከመናፍስት ዓለም መልዕክት የሚመጣለት ሰው ነበር።" ይሉና ስለህልውና አሁን የትነው ለሚለው ጥያቄ እንዲህ ይክዳሉ "ኢየሱስን አግኝቶ ለማነጋገር በአሁኑ ግዜ ማንኛውም ሰው ይችላል። መንገዱም በእምነት ቦታችን መምጣትና በምጡቅ ተመስጦ (Meditation) ውስጥ መግባት ብቻ ነው የሚያስፈልገው። ምክንያቱም እርሱ በአሁኑ ግዜ በመናፍስት አለም ውስጥ አለና ነው" ብለው ያስተምራሉ።

### ሐ) <u>ስለ መንፈስ ቅዱስ</u>

ይህ የክህደት እምነት ስለመንፈስ ቅዱስ የጠለቀ ትምህርት ባይኖረውም በመናፍስት ዓለም ያለ ያንድ ሰው መንፈስ ነው ይላሉ።

### መ) <u>ድኅነት (Salivation)</u>

በዚህ የክህደት ትምህርት መሠረት ድኅነት በመንፈስ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ መድረስ ነው ብለው ማስተማር ነው። የመለወጡ ክንዋኔም በመናፍስት ዓለም ውስጥ ነው። ለዚህ ደረጃ ሰው የሚበቃው ደግሞ እውቀት ሲኖረው ነው ይላሉ።



www.ethiopianorthodox.org

ሰ) <u>ስለሰማይና ሲኦል ወዘተ</u>

በቀጥታ ይህ እምነት ህዝቡ ፈሪሃ እግዚአብሔር ተዘክሮ ሞት የዘላለማዊ ሕይወት ኑሮን እንዳያስብና እንዳይኖረው በማስተማር ስለሰማይ ሲኦል ቅጣት ኃጢያት ወዘተ ማሰብ በፍርሃት የመሸበር በአእምሮ የመደንዘዝ ውጤት ነው ይላሉ።

ረ) <u>ልዩ ልዩ ስርዓቶቻቸው</u>

የዚህ እምነት ተቀዳሚ ተግባር ከመናፍስት ዓለም ጋር ማግኘት ማድረግና መልዕክት መቀበል በጉባኤ ቤታቸው ይከናወናል። ሐዋርያው "ሰይጣን እራሱ የብርሃን መልአክ እስኪመስል እራሱን ይለውጣል" [illegible] ኢየሱስ መልዕክቱን ላከልን ወዘተ እያሉ ከመናፍስት ዓለም ሳይሆን በማለት ህዝቡን ያደናግራሉ።

በመሰብሰቢያ ስፍራቸውም ስለምጡቅ ተመስጦ እምነት እንዲለማመዱ አጥብቀው ያስተምራሉ። ይህንን በተጋጋለ መዝሙርና መዝሙር ውስጥ ነው የሚያከናውኑት በሰለጠነው ዓለም ልዩ [illegible] ምሬት ለማየት የሚፈልጉ፣ ከመናፍስት ዓለም የሚመጣውን መልዕክት መቀበል የሚፈልጉ፣ በህይወት ከሌላ ዘመዶቻቸው የትዳር ጓደኞቻቸው ጋር ወዘተ ለመገናኘት ተስፋ የሚያደርጉ ሰዎች ወደዚያ ለመሔድ ከፍተኛ ፍላጐት አላቸው። ጠንከር ያለው ዓላማውም ዘመናዊውን [illegible] በክርስትናው ሽፋን መፈሀም ነው።



ሠ) <u>መጻሕፍትን</u>

ድርጅቱ ኑፋቄውን በክርስትና ስም ቢሰይመውም መጽሐፍ ቅዱስን አይጠቀምም። ነገር ግን ለማስመሰል "የኢየሱስ ወንጌል፣ ስፕሪቹዋሊስት" እንዲሁም "መጽሐፍ ቅዱስ" በማለት የፈጠራ ድርሰት በመጨመር የተወሠነ መጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በመውሰድ ይጠቀሙበታል።

እንግዲህ ሰይጣን ለዓመፅ ግብሩ ሰውን በማነሳሳትና በመሳሳት እሚፈፅመውን ጥፋት ማስተዋል ይገባል። እነዚህ የተመለከትናቸው የክህደት ድርጅቶች ደግሞ የተነሱት ሁሉም ቅጥ ያጣውን የፕሮቴስታንት አካሔድን ለቀው በመውጣት ወደበለጠው ጥፋት የገቡ ናቸው። በመቀጠል ደግሞ የክርስትናን ስም ሳይዙ ነገር ግን ስህተትን ለሚያስተምሩ የተወሰኑ እምነቶች በመጠኑ እንመለከታለን።

## 5.8 <u>የይሖዋ ምስክር (Johova Witnes)</u>

### <u>አመሰራረቱ</u>

ይህ ድርጅት ዋችታወር ሶሳይቲ (watchtower society) ተብሎ የሚጠራ አርዮሳዊ እምነት ያለው በቻርለስ ታዞራስልና በዮሴፍ ኤፍ ሩዘርፎርድ ከ1879 በፔንሲልቫንያ የተቋቋመ ድርጅት ነው። ዛሬ "መጠበቂያ ግንብ" የተባለውንና ሌሎች የማሳሳቻ ጽሁፍን እያሳተመ የሚያሰራጭበትና እምነቱን በማዕከልነት የሚቆጣጠርበት ቦታ (መስሪያ ቤቱ) በብሩክሊን ኒውዮርክ ይገኛል።



www.ethiopianorthodox.org

## ቻርለስ ታዝራስል ማንነው?

ይህ ሰው በፔንሴልቫኒያ (አሜሪካ) በ1852 የተወለደ [illegible] የፕሮቴስታንት እምነቶች ውስጥ በንቃት ይሳተፍ የነበረ ሲሆን ነገር [illegible] በዚህ ቆይታው የፔሪስቤቴሪያን ቤተክርስቲያን አስቀድሞ [illegible] ትምህርትን ስትስጥ በመቸገሩና

- በዘላለማዊ ኩነኔ
- በክርስቶስ ዳግም መምጣት
- አስቀድሞ መመረጥን

አልቀበልም በማለት እግዚአብሔር የለሽ እስኪሆን ደርሶ ነበር። [illegible] በ1881-1896 ባለው ግዜ "የመጠበቂያ ግንብ የመጽሐፍ ቅዱስና [illegible] ማህበር የሚል" ማህበር መሰረተ። ይህ ማኅበር እስከዛሬ የዚህ [illegible] ተከታዮች የሚጠሩበት ስያሜ ነው።

ቻርለስ ፍጹሞ ዘማዊ የነበረና ከሚስቱ ሜሪያ አክሊ [illegible] ከሌሎች ከሚያስተምራቸው ሰዎች ጋር ዝሙት በመፈፀሙና [illegible] በመደብደቡ ሚሪያ አክሊ በፍርድ ቤት ክስ መስርታ አስቀጥታው [illegible] ይህ ሰው በ1916 በቴክሳስ እንደሞተ ይነገራል።

## ድርጅቱ ያሁኑን ስያሜ መች አገኘ?

የዋች ታዋር ሶሳይቲ (የመጠባበቂያ ግንብ ማህበር) አሁን [illegible] የሚጠራበትን የይህዋ ምስክር (Johva witness) የሚለውን ስያሜ [illegible] የቻለው በ1930 -31 ባለው ግዜ ውስጥ ነው። የስያሜውን ምንጭ [illegible] በነቢዩ በኢሳይያስ ትንቢት በምዕራፍ 43፥10 ላይ "እናንተ [illegible] ባርያዬ ምስክሮቼ ናችሁ" የሚለውን በመያዝ ነው። ይሁንና ለአርዮ[illegible] ይህ ስያሜ አይገባቸውም።



ምስክሮቹ የሆኑ ሐዋርያት ወልድ ዋህድ ብለው መሠከሩ፣ የባህርይ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን በመጀመሪያ ቃል ነበር ቃልም እግዚአብሔር ነበር እያሉ ተናገሩ እንጂ ለቃል (ለወልድ) መኖር ጅማሬ ነበረው አላሉም። በመሆኑም ሰይጣን ለጨለማው ሥራው የተጠቀመበት ሀሰተኛ የብርሃን ጭላንጭል ነው። ስለዚህ አንባቢ አርዮሳውያን የሚለውን መጠሪያ ሊጠቀምበት ይችላል።

## ትምህርተ ክደታቸው

### ሀ) ስለፈጣሪ ያላቸው ትምህርት

ይህ እምነት ቀጥታ አርዮሳዊ በመሆኑ በስላሴ አያምንም። "አንድ አካል አለ እሱም ይሆዋ ነው" ይላሉ። እንደውም በተለያዩ የክህደት ጽሑፎቻቸው ስለስላሴ (ስለአንድነትና ሶስትነት) የሚያስተምረውን ትምህርት በተለያዩ የፈጠሩ ጽሑፎቻቸው በመተካት መጽሐፍ ቅዱስን እየበረዙ ይገኛሉ። ክርስቲያኖችን በብዙ አማልክት እንደማያመልኩ ለማስመሰል በተለያዩ ግዜ የክህደት ጽሑፍን ምስልን እያስደገፉ ያሰራጫል። ቤተክርስቲያን ስለስላሴ ያላትን አስተምሮ በገጽ በጥንቃቄ ይመልከቱት ያጥኑትም።

### ለ) ስለ ክርስቶስ

አርዮስ በኒቂያ የተወገዘበት ክህደቱ ወልድ ፍጡር በመለኮቱ የሚለውን ድርጅቱ ተቀብሎ በቀጥታ ያምንበታል። ከዚህም ጋር

- "ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ አምላክ አይደለም (God head) ነገር ግን ከእግዚአብሔር የሚያንስ አምላክ (a god) ነው ይላሉ።"



www.ethiopianorthodox.org

- የፍጥረት ሁሉ በኩር ነው።
- ኢየሱስ ክርስቶስ የመላዕክት አለቃ ሚካኤል ነው። በምድር [illegible] ከመኖሩ በፊት ሚካኤል ነበር። ትንቢተ ዳንኤል 12፥1 ላይ የተነገረው የተፈፀመው ኢየሱስ በሰማይ በነገሰበት በ1914 ዓ.ም. ነው [illegible] ይህንንም you will be done on earth በተባለው ጽሑፋቸው ጽፈውታል። ገጽ 259-60 1994 እ.ኤ.እ.
- የኢየሱስ ትንሣኤ በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ ነው ሥጋው በ[illegible] ጠፍቷል። ወይም ጋዝ ሆኗል ይላሉ። በግርማ መንግሥቱ [illegible] ትስብዕቱ አይመጣም ይላሉ።

የቤተክርስቲያንን ትምህርት ስለዚህ ክህደት ምላሽ ምን እን[illegible] በገጽ __ ይመልከቱ።

ሐ) <u>ስለ መንፈስ ቅዱስ</u>

ይህ እምነት መንፈስ ቅዱስ አካል ያለው አይደለም። ነገር ግን ዝርው ኃይል ነው። ይልቁንም ረቂቅና የይሆዋ ኃይል ነው እንጂ [illegible] ያለው አይደለም ይላሉ። ስለመንፈስ ቅዱስ የቤተክርስቲያን ትም[illegible] በሙሉ አይቀበሉም። በጸጋውም አያምኑም። የቤተክርስቲያንን ትም[illegible] በገጽ __ ይመልከቱ ያጥኑትም።

መ) <u>ድኅነት (Salivation)</u>

ይህ ድርጅት ላይ ስለክርስቶስ አዳኝነት አምናለሁ ቢልም [illegible] "ፍጡር" ብሎ አዳኝ ማለት የተዛባና ሰይጣናዊ አሰራር ከመሆኑም [illegible] የጌታን ደም ከንቱ ማድረግ ነው። ፍቅሩንም ማናናቅ ነው። ስለዚህም [illegible] ይህ የክህደት ድርጅት በጸጋው ከመደገፍ በድርጅቱ የዕለት [illegible]



እንቅስቃሴ ሥራ ላይ መደገፍ ድኅነትን እንደሚያስገኝ የሚያምነው ተከታዮቻቸውንም የዋችት ታዋርን ሕግ መጠበቅ መኖርን እንዲለማመዱ ያበረታቷቸዋል እንጂ በክርስቶስ ስለተገኘው ድኅነት ግድ አይሰጣቸውም። ለዚህም ነው "በምድር ለዘላለም መኖር ትችላለህ" በሚለው ትምህርት ተከታዮቻቸውን ጠርንፎ በመያዝ የጌታን ማዳን ከንቱ ለማድረግ የሚሯሯጡት።

ሁሉም እንደሚያውቀው ምድርን ስለመውረስ በጀሆቫዎች ጠንከራው ያስተምራሉ። 144,000 ሰዎች መነጠቅንም ይሰብካሉ። ለግንዛቤ እንዲሆን ይህን ትምህርተ ክህደት በመጠኑ እንመለከተዋለን።

በጆሆቫ እምነት የዳነው ሕዝብ በሁለት ይከፈላል። እነርሱም ቅቡዓ ንና ታላቁ መንጋ

ሀ) ቅቡዓን የሚባሉት 144,000 የሆኑ የእግዚአብሔር የመንፈስ ልጆች ሆነው በሰማይ የሚኖሩ ናቸው። ለትንሳኤ ይነጠቃሉ፡

ለ) ታላቁ መንጋ የሚባሉት ደግሞ ትንሣኤ ካገኘ በኋላ በምድር ላይ ለዘላለም ለመኖር የሚችሉ ናቸው ብለው ይከፍሏቸዋል።

ቅቡዓኑ እንደ እምነቱ ትምህርት በ1935 ዓ.ም. 144,000 ቁጥሩ ሞልቷል ይሁንና ለ5ሺ ሰዎች ግን ጥቂት ቦታ ብቻ አለ ብለው የሾፈት የተረት ቃል ያስተምራሉ።

ይሁንና ባለራዕዩ ዮሐንስ ስለ 144,000 ሰዎች የተናገረው ቃ[illegible] ፈጽሞ ከዚህ የስህተት ትምህርት ጋር የማይያያዝ መሆኑን ልብ ሊባ[illegible] ይገባል።



www.ethiopianorthodox.org

ሰ) **<u>ስለድንግል ማርያም</u>**

ስለወላዲተ አምላክ ድርጅቱ ታላላቅ ኑፋቄን ያስተምራል፦

1)የፍጡር እናት ይሏታል።

2)ዘላለማዊ ድንግል መሆኗን ይክዳሉ።

3)ክብሯን አማላጅነትና እናትነቷን የመስቀል ስጦታነቷን በአጠቃላይ ቤተክርስቲያን ስለእመቤታችን የምታስተምረውን ይክዳሉ።

ረ) **<u>ስለመላዕክት</u>**

ስለቅዱሳን መላዕክት ከእግዚአብሔር ቃል ፍጹም ልዩ የሆነ ክህደትን ያስተምራሉ።

1. በደብር ቅዱስ ደቂቀ ሴትና ደቂቀ ቃየል የወደቁበትን የዘመኑትና ልዩ ኃጢያት መላዕክት ከሰው ጋር እንደፈፀሙት ያስተምሩበታል። በወንጌል ጌታ መላዕክት አያገቡም አይጋቡም ያለውን ቃል አይቀበሉም።
2. ሚካኤል ኢየሱስ ነው ይላሉ። በትንቢተ ዳንኤል የተጠቀሰው የመላዕክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የሚያዛምድ ነገር የለውም። ነቢያት ከሙሴ ጀምሮ እነ ኢሳይያስ፣ ሕዝቅኤል፣ ኤርሚያስ፣ ዳንኤል፣ ሚክያስ፣ ዘካርያስ ወዘተ ስለጌታ ትንቢት ተናግረዋል። ነገር ግን በመልአክ መልክ ሬዕየ አልተነበዩለትም የሚመጣው መሲህ መልአክ ነበር ብለውም አላስተማሩም። እርሱ የመላዕክት ፈጣሪ ነውና። አርዮሳውያን ሚካኤል ኢየሱስ ነበር ካሉ ኢየሱስ ሰው ሲሆን ሚካኤል የት ሔደ ኢየሱስ ሰው ሆኖ ወደምድር መጥቶም ስለመላዕክት አለቃ ስለ ቅዱስ ሚካኤል የተፃፈውን በሀዲስ ኪዳን ተጠቅሶ እናገኘዋለን "ጌታ ራሱ በትዕዛዝ በመላዕክትም አለቃ ድምጽ በመለከት ከሰማይ ይወርዳልና" (1ተሰ.4፥16) ይለናል። በምጽዓት ግዜ መለከት ከሚነፋውና የምጽዓቱን



ነገር ከሚያውጀው አንዱ ሊቀመላዕክት ሚካኤል ነው። በምጽዓት ለፍርድ እሚመጣው ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

እንዲሁም የያዕቆብ ወንድም ይሁዳ በመልዕክቱ የመላእክት አለቃ ሚካኤል ስለሙሴ ሥጋ ከዲያብሎስ ጋር እንደተከራከረ በገለጠበት መልዕክቱ ላይ ሚካኤል ኢየሱስ ቢሆን ኖሮ ገልፆ ይጽፈው ነበር። ነገር ግን ሐዋርያት መላእክትን ከመላእክት ጌታ ለይተው ስለሚያውቁ እየለዩ ጽፈዋል።

ቅዱስ ጳውሎስም በዕብራውያን መልዕክቱ ከመላእክት ወገን አንተ ልጄነህ ተብሎ የተጠራ ያለመኖሩንና የመላዕክቱንም አገልግሎት ዘርዝሮ መፃፉ ከመላእክት ሥጋን ይለብስ ዘንድ የተገለጠ አለመኖሩንና በፍጡር ደም የሰው ልጅ ነፃ መውጣት ስለማይችል፤ በሥጋ የተገለጠው የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ነቢያትም የሚከተለውን በተለያየ ዘመን ስለእርሱ ተንብየው ነበር። ይህም ሥጋ ከመልበሱ በፊት የተነገረ ነበር። ሥጋ ለብሶ ሲገለጥ ትንቢተ ነቢያትም በሙሉ ተፈፀም።

ኢሳይያስ ከድንግል መወለዱን (ኢሳ.7፥14)፣ ሚክያስ በቤተልሔም ስለመወለዱ (ሚክ. 5፥2)፣ ሆሴዕ በግብጽ ስለመሰደዱ (ሆሴዕ 11፥1)፣ ዳዊት የእግዚአብሔር ልጅ በሥጋ ስለመገለጡ (መዝ.109፥1)፣ ስለመከራ መስቀሉ (መዝ.21፥1-24፤ ኢሳ.53፥1-12)፣ መሞቱን፣ መነሳቱንና ማረጉን (ኢሳ.53፥1-2፤ መዝ.7፥76፤ መዝ.46፥5፤ መዝ.42) እነዚህ ሁሉ ትንቢቶች የእግዚአብሔር ልጅነቱን እንጂ መላዕክት መሆኑን ፈጽሞ አያመለክቱም። ከዚህ የተለየ የሚያስተምሩ ግን የኢጋንትን ትምህርት እሚያዳምጡ መሆኑን ልብ ይለዋል።



www.ethiopianorthodox.org

## ማጠቃለያ

## መናፍቃን እንዴት ክርስቲያኖችን ያጠምዳሉ?

መናፍቅነት የሥጋ ሥራ ነው። ይህንን የሥጋ ሥራ ደግሞ አስቀድሞ ስቶና ወድቆ የነበረው ጠላት በማህበረ መላእክት መካከል ፈጣሪውን ክዶ ጥርጥርን እንደዘራ፣ በወንጌል ጌታ እንዳስተማረን በንጹህ ስንዴ ዘር ላይ እንክርዳድ የዘራ ጠላት መሆኑን እንደገለጠልን ሁሉ ዲያብሎስ ሁል ግዜ ይህንን አመጽ ለማድረግ ይተጋል።

በመሆኑም የመናፍቃን አቀራረብን ክርስቲያኖች ጠንቅቀው እንዲያውቁት በመጠኑ እንጠቁማለን።

### 1. የይሆዋ ምስክር (ጆሆቫ ዊትነስ)፡-

እነዚህ መናፍቃን በየመንገዱ ቦርሳ አንጠልጥለው እንደምናውቃቸውና እንደሚያውቁን ሰላምታ በመስጠት "ስለዘላለማዊ ሕይወት ምን ታስባለህ በማለት" ውይይቱን ይጀምራሉ። እንዲሁም በእጃቸው የያዙትን የድርጅቱን መርሀግብርና አስተምሮ የሚያጋልጥና በስላሴ ማመንን የሚነቅፍ ትራክቶችን እንድንገዛ ይጋብዙናል። የለሰለሰው አቀራረባቸውን ስንመለከት ጌታ "የበግ ለምድ ለብሰው ይመጣሉ" ያለው ሁል ግዜ ትዝ ሊለንና ልናስበው ይገባናል። እነዚህ መናፍቃን ብዙውን ግዜ በሆስፒታል፣ አካባቢ በተለያዩ መዝናኛዎች አካባቢና ሰው በተለያዩ ሃሣብ ሊጠመድ በሚችልበት ቦታ ማተኮር ይወዳሉ። በተለይም እድሜያቸው የገፉ ሰዎች ሳይቀሩ ለዚህ ጥፋት ስለሚሰለፉ በተቻለ መጠን መጠንቀቅ ተገቢ ነው። ይልቁንም ያልበሰለ ምዕመን ከእነዚህ ጋር ግዜውን ያሳልፍ ዘንድ አይገባውም።

### 2. ፕሮቴስታንት

ብዙውን ግዜ እንደምንመለከተው ፕሮቴስታንቶች የኦርቶዶክስ አማኝን ለመሳብና ለመለወጥ እሚጠቀሙበት መንገድ ቤተክርስቲያ ክርስቶስን እንደማታውቅ በባህል እንደተያዘች፣ አገልጋዮቿችን በስህተት የተያዙ ወዘተ አስመስለው የፈጠራ ወሬን በማውራት ነው።

ከአሜሪካን ሀገር እየታተመ የሚሰራጨው Gospel Tract and Bible Society የሚለውን የሚያዘጋጁት አካላት "እንዴት ለኦርቶዶክሳውያን እንመስክርላቸው" በሚለው ጽሁፋቸው

- ለግዜው ስለማርያምና ለቅዱሳን አለማንሳት፣
- ኢየሱስ የግል አዳኝ መሆኑን ማስጨበጥ፣
- እነርሱ ፈልገው ካልሆነ በተለያዩ የቤተክርስቲያን ሥርዓት ላይ አለመወያየት፣
- የዮሐንስን ወንጌልና ዕብራውያን ላይ አትኩሮ መነጋገር፣
- በቤተክርስቲያናቸው ሆነው ለውጥ እማያመጡበትን ማመቻቸትን ያስፈልጋል ይላሉ።

ከዚህም ጋር አጫጭር የሆኑ ጽሑፎችና የመዝሙር ክር በማቅረብ ለመሳብ ከፍተኛ ጥረት ከማድረግ ጋር ቤተክርስቲያኒቷ የሚገጥማትን ወቅታዊ የሆኑ ችግሮች ያለመግባባቶች ወዘተ ለመስበክያ አዘውትረው ይጠቀሙበታል። በወቅታዊ ሁኔታዎች የምስክርነት ጊዜ



www.ethiopianorthodox.org

በማለትና ኮንፈረንስ የሀሎት ጊዜ የፈውስ ሰዓት፣ የአምልኮ ሥርዓት ወዘተ በማለት ኦርቶዶክሳዊያንን ያጠምዳሉ።

## 3. የሮማውያን አቀራረብ

የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ተደጋግሞ እንደምንሰማው አስተዳደራዊ (Administration) እንስቃሴዋ የበሰለ በመሆኑ እንደ ፕሮቴስታንት ከመስበክ ይልቅ ሚሲዮኖቿ የገጠሩን ማህበረሰብ ባህል ቋንቋ... አጥንቶና በተለያየ እርዳታ ሰበብ ሕዝቡን መያዝ ተቀዳሚ ተግባራቸው ነው። ብዙውን ጊዜ "አንድነን" የሚለው ቋንቋቸው ደግሞ የሚያዘናጋ በመሆኑና አጠንክሮ የሚቃወምም ስለማይኖር በቀላሉ ለመወረርና በረጅም ዓመታት የማያመጡትን ውጤት ሁልግዜ አልመው ይንቀሳቀሳሉ።።



## ዋቢ መጻሕፍት


- **ወንጌል ቅዱስ ንባብና ትርጓሜ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት፣** 1988
- **የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፣ አ.አ.** 1972
- Themoty ware - The Orthodox Church, London 1963
- Dr. Poul P.Enns - Historical Theology, Chicago U.S.A, 1989
- Dictionary of Pentecostal and Charsmatic movement regence publisher grand rapidsm, 1988.
- Jane Markisen -666 U.S.A. 1998 Chicako.
- Catholic Twin Circle, August 25, 1985 Art Saciety.
- Catholic Church, The renaissance and protestantism, Agu 25, 1997
- The four majorcults, (grand rapid) Erdmans, 1982.
- **ከቀደስ አለማየሁ ሞገስ ደራሲ፣ አንድ እረኛ አንድ መንጋ፣ ንግድ ማተሚያ** 1989 **አ.አ.**
- **ተስፋዬ ሮበሌ የይሖዋ ምስክሮች አስተምሮዎአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን፣ ራእይ አሳታሚ አ.አ.** 1993
- **በምድር ላይ በገነት ለዘላለም መኖር ትችላለህ** Watchtower Bible and Tract Society, 1991.
- Basic Christian doctrine, ed. Carl F. Henry. Grand rapids, Baker, Book house 1993.
- **የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መካነ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን መተዳደሪያ ደንብ፣** 1993፣ **አ.አ.**




www.ethiopianorthodox.org